የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት




# በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ምርምር ሥራዎች እና የምርምር ፈንድ አጠቃቀም በተመለከተ የተከናወነ የአካባቢ ኦዲት ሪፖርት



መጋቢት/ 2015 ዓ.ም

## መውጫ


ክዋኔ ኦዲቱ ማጠቃለያ ..... iii

**ክፍል አንድ** ..... 1

**መግቢያ** ..... 1

የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮ እና ራዕይ፡- ..... 2

ተልዕኮ ..... 2

ራዕይ ..... 2

የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች ..... 3

ዩኒቨርሲቲ ድርጅታዊ መዋቅር፡- ..... 3

አደረጃጀት ..... 3

የጥናትና ምርምር የሥራ ክፍል ድርጅታዊ መዋቅር ..... 3

የዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል ..... 4

የፋይናንስ ምንጭ ..... 5

የኦዲቱ ዓላማ ..... 6

የአካባቢ ኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) ..... 6

የኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርት ..... 6

የኦዲቱ ወሰን፡- ..... 6

የኦዲቱ ዘዴ ..... 7

**ክፍል ሁለት** ..... 8

**የኦዲት ግኝቶች** ..... 8

የምርምር ጭብጦችን በየአምስት ዓመቱ የሚለዩ መሆኑን በተመለከተ፡ ..... 8

የምርምር ስራዎች የህብረተሰቡን ፍላጎት መነሻ ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ፡- ..... 9

በአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ላይ ጥናትና ምርምር መደረጉን በተመለከተ ..... 11

በባቢሌ ወረዳ፡- ..... 11

ምርምር ሥራዎች የአገር በቀል እውቀት ላይ ያተኮሩ መሆኑን በተመለከተ፡ ..... 13

የምርምር ሥራዎቹ የአካባቢ ብክለትን መከላከልን ያካተተ መሆኑን በተመለከተ፡- ..... 14

የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ ክትትልና ግምገማ መደረጉን በተመለከተ፡- ..... 16

ለምርምር ስራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እየቀረበ መሆኑን ተመለከተ:- ..... 20

ኮንትራት በሚገቡ ተመራማሪዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፡- ..... 21

የምርምር ውጤት ርክከብ ማድረጋቸውን በተመለከተ፣ ........ 22
የምርምር ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ ሥርዓት መዘርጋትን በተመለከተ፡- ........ 23
የምርምር ውጤቶች የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ስርዓትን በተመለከተ፡- ........ 24
ዘመናዊ የቤተሙከራ መደራጀቱን በተመለከተ፡- ........ 25
ዩኒቨርሲቲው የሐራማያ ሐይቅ ደህንነት ለመጠበቅ መስራቱን በተመለከተ፡- ........ 27
በዩኒቨርሲቲው የወጡ የምርምር ውጤታማነትን በተመለከተ፡- ........ 31
**ክፍል ሶስት** ........ 32
**መደምደሚያ** ........ 32
**ክፍል አራት** ........ 36
**የማሻሻያ ሃሳቦች** ........ 36

**የዩኒቬርሲቲው ድርጅታዊ መዋቅር አባሪ-** 1 ........ 39
**አባሪ- 2** ........ 40
የጥናትና ምርምር የሥራ ክፍል ድርጂታዊ መዋቅር ........ 40
**የኦዲቱ ጭብቶችና መመዘኛ መስፍርት** ........ 41
የሀረማያ ዩኒቬርሲቲ ስድስት ዋና ዋና የምርምር መስኮች ........ 46

## የኦዲቱ ማጠቃለያ

በሀገራችን አንጋፋ ከሆኑት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል አንዱ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ በ509 ኪ.ሜ ርቀት በሐረርና ድሬደዋ ከተሞች መካከል ይገኛል፡፡ የኢትዮጵያ ትምህርት በተለይ ግብርናን ዘርፍ ለማዘመን ቀዳማዊ ኃይል ሥላሴ በነበራቸው ፍላጎት በ1942 ዓ.ም የዛሬው ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የእርሻና መካኒክ ጥበብ ኮሌጅ በሚል ከተቋቋመ ጀምሮ፤ በተለይም በግብርናው የምርምርና ስርጸት ዘርፍ ፈር ቀዳጅ ሲሆን፤ በዘርፉም በርካታ ተመራማሪዎችን ያፈራና የምርምር ውጤቶችን፣ ቴክኖሎጂዎችን እና የፖሊሲ ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ በማላመድና በማሰራጨት የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የዩኒቨርሲቲው የአካባቢ ጥበቃ ሥራዎች፣ ምርምር እና የምርምር ፈንድ አጠቃቀም ውጤታማ በሆነ መልኩ ማከናወኑን ለማረጋገጥ በሥራው ዙሪያ የሚታዩ የአሠራር ክፍተቶችን እና የችግሮቹን መንስኤ በመለየት የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲጠናከር ለማድረግ ይህን የክዋኔ ኦዲት አካሂዷል፡፡

የአካባቢ ኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) የአካባቢ ጥበቃ ምርምር ስራዎች(Environmental research) ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣ የምርምር ሀብት አያያዝና አስተዳደር ውጤታማነት መገምገም እና የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚው ተደራሽ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን መገምገም ናቸው፡

የክዋኔ ኦዲቱ የተከናወነው በአለም አቀፉ የዋና ኦዲተሮች ማህበር የተዘጋጀውን አለምአቀፍ የክዋኔ ኦዲት ስታንዳርዶች (ISSAI 300/3000) መሰረት እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን ነው፡፡ ዝርዝር ኦዲቱ የሸፈነው ከ2009 እስከ 2015 የመጀመሪያው ሩብ ዓመት ድረስ ያሉ የሥራ ክንውኖችን ነው፡፡

በመሆኑም በክዋኔ ኦዲቱ የታዩ ዋና ዋና ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- ✓ የሀረማያ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ ቁጥር 1/2011 ዓ.ም እና በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ሊጅስትሌሽን ላይ በተጠቀሰው መሠረት ትኩረት የሚሹ ጭብጦችን በየአምስት ዓመት ወቅታዊ በማድረግ በትኩረት

መስኩ ተካተው ምርምር ሊከናወንባቸው የሚፈለጉ አጀንዳዎች እንዲካታቱ ያልተደረገ መሆኑ፣

- ✓ በምስራቅ ሀረርጌ ከፍተኛ የፀረ-ተባይ ዝቃጭ በውሃ እና በጫት ምርቶች ላይ መኖሩን በጥናትና ምርምር የተለየ ቢሆንም ኬሚካሉ በሰውና በእንሰሳት ላይ የመጣው ዐሉታዊ ተፅዕኖ ተገምግሞ በሌላ አማራጭ ኬሚካል እንዲተካ ለማድረግ ያልተሠራ መሆኑ፣
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በሀረር ጤና ኮለጅ፣ ሕይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል እና ሐርሜ (የማይጅ) ጠቅላላ ሆስፒታል የሚወጡት ፈሻስ ቆሻሻዎች ማስወገጃ ፕላንት (Treatment plant) ባለማዘጋጀቱ አልፎ አልፎ የቆሻሻ ማከማቻ ታንከሮቹ እየሞሉ ወደ ማህበረሰቡ እየተለቀቀ ቅሬታ እየተፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም ደረቅ የሕክምና ቆሻሻዎችን ለማስወገድ የሚያስችል ኢኒስኔሬተር ባለመኖሩ አካባቢን ሊበክል በሚችል መልኩ ክፍት ቦታ ላይ በማቃጠል እንዲወገድ እየተደረገ መሆኑ፣
- ✓ በውጪ የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች የአፈፃፀም ሪፖርታቸውን ምርምሩን ለሚመሩት የሥራ ክፍሎች እና ለዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር ቀርቦ የማይገመገሙ መሆኑ፤ እንዲሁም ከግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች በዩኒቨርሲቲው የፕሮጀክት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ተመዝግቦ አፈፃፀማቸው ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግበት መሆኑ፣
- ✓ በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ ውስጥ ከ100 በላይ ቤተሙከራ ሲኖሩ ከነዚህ ውስጥ 20ዎቹ የምርምር ቤተሙከራ ለማድረግ በልይታ ላይ የሚገኙ ቢሆንም ሁሉም በየጊዜው ወቅታዊ(Calibration) የማይደረጉ መሆናቸው፣
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በሀረማያ ሀይቅ ዙሪያ የሚደረጉ የውሃ አጠቃቀሞች የሀይቁን ደህንነት፣ የአፈርንና የእጽዋትን ዕርጥበት መሰረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በጥናትና ምርምር ያመላከተ ቢሆንም የምርምር ውጤቱ ከሀረማያ ከተማ አስተዳደር እና ከወረደ አስተዳደር ጋር ተግባራዊ ለማድረግ ከማህበረሰቡ ድጋፍ ባለማግኘቱ በሀይቁ ጥበቃ እና እንክብካቤ ዙሪያ ችግሮች እየተስተዋሉ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

**በመሆኑም፡-**

- ✓ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ እና በዩኒቨርሲቲው በተዘጋጀው ሴኔት ሊጅስትሌሽን መሠረት በአካባቢ፣ በክልል እና በብሔራዊ ደረጃ ቅድሚያ የሚሹ ችግሮችን በዳሰሳ ጥናት በመለየት የምርምር ጭብጦችን በየአምስት ዓመት ወቅታዊ በማድረግ ችግር ፈቺ ምርምሮችን በማከናወን ለአገሪቱ የበለጠ አስተወፅኦ ሊያበረክት ይገባል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በሀረር ጤና ኮለጅ፣ ሕይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል እና ሐርሜ (የማይጅ) ጠቅላላ ሆስፒታል የሚወጡት ፈሻስ ቆሻሻዎች ለማስወገድ የሚያስችል ፕላንት(Treatment plant) እና ደረቅ የሂክምና ቆሻሸዎችን ለማስወገድ የሚያስችል ኢኒስኔሬተር በማዘጋጀት ቆሻሻዎች አካባቢን በማይበክል መልኩ እንዲወገድ ሊያደርገው ይገባል፡፡
- ✓ በመንግስት በጀትም ሆነ በውጭ የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶችን በተመለከተ በዩኒቨርሲቲው የፕሮጀክት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ እንዲመዘገቡ በማድረግ የፕሮጀክቶቹን ፊዝካልና ፋይናንሻል አፈፃፀም ሪፖርት ምርምሩን ለሚመሩት የሥራ ክፍሎች እንዲያቀርቡ በማድረግ ጠንከር ያለ የክትትል እና ግምገማ ሥራ ሊከናወን ይገባል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በሀረማያ ሀይቅ ዙሪያ በርካታ ጥናትና ምርምሮችን የሀይቁን ደህንነት ለመጠበቅ የተፋሰስ ልማቶችን ያከናወነ ቢሆንም፤ ከሚመለከታቸው የሀረማያ ከተማ እና ወረዳ አስተዳደር ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር የምርምር ውጤቱ በማሕበረሰቡ ዘንድ ወርዶ ባለመተግበሩ ሀይቁን ለደግም ጥፋት/መድረቅ በሚደርግ መልኩ ከአቅም በላይ አጠቃቀሞች መኖሩ ተስተውሏል፡፡ በመሆኑም ዩኒቨርስቲው ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር ግንኙነት በመፍጠር በሀይቁ ላይ ተደቀነው ከአቅም በላይ የውሃ አጠቃቀም እንዲሻሻል እና የተፋሰስ ልማቱ በተጠናከረ መልኩ የሚቀጥልበት ሁኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

***መግቢያ***

1. በሀገራችን አንጋፋ ከሆኑት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት መካከል አንዱ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ከአዲስ አበባ በስተምስራቅ በ509 ኪ.ሜ ርቀት በሐረርና ድሬደዋ ከተሞች መካከል ይገኛል፡፡ የአትዮጵያ ትምህርት በተለይ ግብርናን ዘርፍ ለማዘመን ቀዳማዊ ኃይል ሥላሴ በነበራቸው ፍላጎት በ1942 ዓ.ም የዛሬው ሐረማያ ዩኒቨርሲቲ የቀድሞው የኢትዮጵያ ንጉሰ ነገስት መንግስት የእርሻና መካኒክ ጥበብ ኮሌጅን ለማቋቋም መሠረት የሆነው ሀሳብ በንጉሰ ነገስቱ ቀረበ፡፡ በወቅቱ ንጉሱ የኦክሎሀማ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዘዳንት ሄነሪ ቤኔትን ባገኙበት አጋጣሚ ከአሜርካ መንግስት ጋር በነበራቸው ፖይንት ፎር የተባለ የትብብር ስምምነት መሠረት የምርምርና ቴክኒክ ድጋፍ እንዲደረግላቸውና የትምህርት ተቋም እንዲቋቋም ጥያቄ አቀረቡ፡፡
2. በኢትዮጵያና አሜሪካ መንግስት በሚያዝያ ወር 1944 በተፈረመው የውል ስምምነት ሰነድ መሠረት የኢትዮጵያ ፍላጎት የሚያጠና የግብርና ባለሙያዎች ቡድን ወደ ኢትዮጵያ እንዲመጣ ተደረገ፡፡ ቀዳማዊ ኃይል ሥላሴ የግብርና ቴክኒክ የሚያስተምር ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጅማ እንዲመሠረት እና በሌላ አካባቢ ለሚከፈተው ኮሌጅ ተማሪዎችን እንዲያዘጋጅ ታስቦ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቱን አሁን የጂማ ዩኒቨርሲቲ የሆነውን በመስከረም ወር 1945 ዓ.ም እንዲከፈት ተደርጎ ተማሪዎችን በተግባር የተደገፈ የግብርና ትምህርት መስጠት ተጀመረ፡፡
3. በየካቲት ወር 1945 ዓ.ም ደግሞ የግብርና ኮለጁ የሚቋቋሚበት ቦታ ሐረማያ እንዲሆን ንጉሰ ነገስቱ ቦታውን መርጠው አሳወቁ፡፡ በ1946 ዓ.ም ንጉሱ በመረጡት ቦታ ላይ የኮሌጁ ህንፃ ግንባታ ሥራ ተጀመረ፡፡ የኮለጁ ህንፃ ዲዛየን የኦክሎሀማ ስቴት ዩኒቨርሲቲ አርክቴክቸሮች የግንባታ ስራውን ደግሞ አዲስ አበባ የነበረ ጣሊያናዊ የኮንስትራክሽን ድርጅት በመስራት ግንባታውን በ1948 ዓ.ም አጠናቆ የመጀመሪያዎቹን በ11 ተማሪዎች ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በመቀበል ትምህርት መስጠት ጀምሯል፡፡ በቀጣዩ ዓመት የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎችን በመቀበል የንድፈ ሀሳብና የተግባር ትምህርቶችን በኮሌጁ ግቢና በአካባቢው አርሶ አደሮች ማሳ ላይ ማስተማር የጀመረ ዩኒቨርሲቲ ነው፡፡

4. ዩኒቨርሲቲው ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በግብርና ትምህርት ዘርፍ በሁለት የትምህርት ፕሮግራሞች የመማር ማስተማሩን ሂደት የጀመረው ባለፉት ስድስት አስርተ ዓመታት በተለያየ የትምህርት ዘርፎች ለማስፋፋት ባደረገው ጥረት በአሁኑ ወቅት በ9 ኮሌጆች፣ በአንድ ኢኒስቲትዩት እና አካዳሚክ 229(ሁለቱ በክረምት መረሃ-ግብር ብቻ የሚሰጡ ናቸው፡፡) የትምህርት ፕሮግራሞች በመክፈት እስከ አሁን 122,169 ምሩቃንን በዲፕሎማ፣ በመጀመሪያ ዲግሪ፣ በ2ኛ ዲግሪ እና በ3ኛ ዲግሪ (ፒ.ኤች.ዲ) ያፈራ ተቋም ሲሆን ከምሩቃኑም መካከል በአገራችን እና በዓለም አቀፍ ደረጃ በሥራቸው የታወቁ ሊህቃን ሳይንትስቶችና የአገር መሪዎች ይገኙበታል፡፡
5. ከ1980ዎቹ ጀምሮ ዩኒቨርሲቲው ከግብርና በተጨማሪ ሌሎች በርካታ የትምህርት መስኮች መክፈቱን ተከትሎ የምርምርና ስርፃት ዘርፍ ያደገ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በስድስት የምርምር የትኩረት መስኮችና በ22 ንዑስ ትኩረት መስኮች ስር 216 የምርምር ፕሮጀክቶችን እያካሄደ ሲሆን በያዝነው በጀት ዓመት 76 የምርምር ፕሮጀክቶች አዲስ የፀደቁ ናቸው፡፡
6. ዩኒቨርሲቲው በተለይም በግብርናው የምርምርና ስርጸት ዘርፍ ፈር ቀዳጅ ሲሆን በዘርፉም በርካታ ተመራማሪዎችን ያፈራና የምርምር ውጤቶችን፣ ቴክኖሎጂዎችን እና የፖሊሲ ሃሳቦችን በማፍለቅ፣ በማላመድና በማሰራጨት የማህበረሰቡን ተጠቃሚነት ለማጎልበት የበኩሉን አስተዋጽኦ እያበረከተ ይገኛል፡፡

**የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ተልዕኮ እና ራዕይ፡-**

**ተልዕኮ**

7. በተለያየ የትምህርት መስኮች ተወዳዳሪ የሆኑ ምሩቃንን ማፍራት፣ ችግር ፈች ጥልቅ ምርምሮችን ማካሄድ፣ ቴክኖሎጂዎችንና እውቀትን በማፍላቅና በማሰራጨት ለአካባቢያዊ፣ ለብሔራዊ፣ ለክልላዊ እና ለአለም አቀፍ ዘላቂ ልማት አስተዋፅኦ የሚያበረክቱ የማህበረሰብ ፍላጎትን ላይ የተመረኮዙ ዘላቂ ለውጥ የሚያስገኝ ተሳትፎን ማረጋገጥ፤

**ራዕይ**

8. በመማር ማስተማር፣ በምርምር እና በማህበረሰብ አገልግሎት በ2030 እ.ኤ.አ በምስራቅ አፍሪካ ካሉት አስር ግንባር ቀደም ትላልቅ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ መሆን ነው፣

**የከፍተኛ ትምህርት ዓላማዎች**

9. የከፍተኛ ትምህርት የሚከተሉት ዓለማዎች ይኖሩታል፡-
   - የአገሪቱን ልማት፣ ሠላምና ዲሞክራሲ ሥረዓት ግንባታ ዕውን የሚያደርጉ፣ ህብረ ብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አንድነት የሚያጎለብቱ የማንነት፣ የባህልና የታሪክ ብዝሃነትን የሚንከባከቡ እንዲሁም ሃገሪቱን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተወዳዳሪ መሆን ሚያስችሏት ምሩቃንን ማዘጋጀት፣
   - በአገሪቱ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ችግር ፈቺ የሆነና በዕውቀትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ያተኮረ ምርምርን ማራመድና ማጎልበት፣
   - በተልዕኮው እና በመልካም አስተዳደር የልህቀት ማዕከል ሆኖ ለአገራዊ ሥራዎች ስኬት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ተቋማዊ ቁመና መፍጠር፣ መገንባትና ማጎልበት፣

**ዩኒቨርሲቲ ድርጅታዊ መዋቅር፡-**

**አደረጃጀት**

10. ዩኒቨርሲቲው ተጠሪነቱ ለትምህርት ሚኒስቴር ሲሆን በበላይነት በቦርድ የሚተዳደር እና በአንድ ፕሬዝዳንት የሚመራ ሆኖ በስሩ ሁለት ካውንስል፣አንድ ሴኔት፣ ሦስት ምክትል ፕሬዝዳንት እና ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዝዳንት ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ ስድስት ዳይሬክቶሬቶች እንዲሁም ሦስት ለዋና ፕሬዜዳንት ተጠሪ የሆኑ ጽ/ቤቶችን በመያዝ የተዋቀረ ነው፡፡ (ዝርዝሩ በአባሪ -1 ተያይዟል)

**የጥናትና ምርምር የሥራ ክፍል ድርጅታዊ መዋቅር**

11. የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫው የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጥበቃ ምርምር ስራዎች እና የምርምር የፈንድ አጠቃቀም ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም ሲሆን የሥራ ክፍሉ የሚመራው በዩኒቨርሲቲው የምርምር ምክትል ፕሬዘዳንት ሲሆን ተጠሪነቱ ለዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ሆኖ በሥሩ አራት ዳይሬክቶሬት ሲኖሩት በእያንዳንዱ ዳይሬክቶሬት ሥር የተለየ የሥራ ክፍሎች አሉ ፡፡ ዝርዝሩን **በአባሪ-2** ይመልከቱ፡፡

**የዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል**

12.የዩኒቨርሲቲው የሰው ኃይል በየበጀት ዓመቱ የተፈቀደላቸው 5680 ሲሆን በሥራ ላይ የለው  የሰራተኛ ብዛት በ2013 ዓ.ም 3097፣ በ2014 ዓ.ም 4080 እና በ2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት 4080 ሲሆን በተጨማሪ የኮንትራት ሠራተኞች እንደአስፈላጊነቱ በየዓመቱ የነበሩት ብዛት በ2013 ዓ.ም 1740፣ በ2014 ዓ.ም 2192 እና በ2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት 2220 ነው፡፡ ዝርዝሩም እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

| **የሥራው መደብ** | **በመዋቅር የተፈቀደ የሰው ኃይል ብዛት በቁጥር** | | | **በሥራ መደቡ ላይ የነበረው/ያለው የሰው ኃይል ብዛት** | | | | | | | | | **የተፈቀደው የሰው ኃይል በሥራ ላይ ካላው ጋር በመቶኛ ሲነጻጸር (%)** | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 2013 ዓ.ም | 2014 ዓ.ም | 2015 ዓ.ም | 2013 ዓ.ም | | | 2014 ዓ.ም | | | 2015 ዓ.ም 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት | | | 2013 ዓ.ም | 2014 ዓ.ም | 2015ዓ.ም 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት |
| | | | | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | ሴት | ወንድ | ድምር | | | |
| **ቋሚ ሠራተኞች** | 5680 | 5680 | 5680 | 2352 | 1745 | 3097 | 2344 | 1736 | 4080 | 2344 | 1736 | 4080 | 54% | 71% | 71% |
| **የኮንትራት መምህራን እና ሌሎች** | **እንደ አስፈላጊነቱ** | | | **334** | **1406** | **1740** | **306** | **1886** | **2192** | **314** | **1906** | **2220** | ------- | ------ | ---- |
| | **ጠ/ድምር** | | | 2686 | 3151 | 4837 | 2650 | 3622 | 6272 | 2658 | 3642 | 6300 | | | |

**የፋይናንስ ምንጭ**

13.ዩኒቨርሲቲው የተሰጠውን ተልዕኮ ተግባራዊ ለማድረግ እና በዕቅድ የያዛቸውን ሥራዎች ለማስፈጸም የሚያስፈልገውን ከመንግሥት በየዓመቱ ከሚመደብ መደበኛ በጀት፣ ከለጋሽ አካላት፣ ከውስጥ ገቢ እና ከኢንተርፕራይዝ ልማት ገቢ የሚያገኝ ሲሆን አፈፃፀሙ ከ2012 እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት በሚከተለው ሰንጠረዥ መሠረት ቀርቧል፡፡

| በጀት ዓመት | የዩኒቨርሲቲው መደበኛ በጀት | | | |
|---|---|---|---|---|
| | የተፈቀደው በጀት | የተስተካከለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ (%) |
| 2012 | 1,093,870,000.00 | 1,235,585,653.15 | 1,233,177,190.36 | 99.81 |
| 2013 | 1,258,266,300.00 | 1,595,850,841.99 | 1,504,960,035.67 | 94.30 |
| 2014 | 1,413,047,000.00 | 2,019,025,549.48 | 2,062,034,413.05 | 102.13 |
| 2015 1ኛ ሩብ ዓመት | 1,271,742,300.00 | 1,363,742,300.00 | 415,463,108.20 | 30.46 |
| | **ለምርምር የተመደበው በጀት** | | | |
| 2012 | 46,000,000.00 | 51,878,583.45 | 51,790,669.81 | 99.83 |
| 2013 | 54,372,700.00 | 66,008,464.12 | 63,199,757.91 | 95.74 |
| 2014 | 62,324,800.00 | 105,548,937.71 | 104,926,673.14 | 99.41 |
| 2015 1ኛ ሩብ ዓመት | 50,000,000.00 | 50,000,000.00 | 8,136,186.43 | 16.27 |
| | **ለምርምር ከለጋሽ ድርጅቶች የተገኘ** | | | |
| 2012 | 60,169,931.00 | | 45,258,822.16 | 75.22 |
| 2013 | 76,834,739.15 | | 53,629,668.50 | 69.80 |
| 2014 | 87,988,163.94 | | 69,273,250.44 | 78.73 |
| 2015 1ኛ ሩብ ዓመት | 49,209,112.97 | | 27,629,609.29 | 56.15 |

**የኦዲቱ ዓላማ**

14.የሀረማያ ዩንቨርሲቲ የአካባቢ ጥበቃ ምርምር ስራዎች እና የምርምር የፈንድ አጠቃቀም ውጤታማ በሆነ መልኩ እየተከናወኑ መሆኑን ለማረጋገጥ ሲሆን የኒቨርሲቲው በሚያከናውነው ምርምሮች ዙሪያ የአሠራር ችግሮች ካሉ ለይቶ በማውጣት ለችግሮቹ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል የማሻሻያ ሀሳቦችን በማቅረብ ምርምሩን ለሚመሩት የሥራ ኃላፊዎች እገዛ ለማድረግና ተጠቂነትንም ለማጠናከር ጭምር ነው፡፡

**የአካባቢ ኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች**

15.ከላይ የተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ(Audit Issues) ላይ የዝርዝር ኦዲት ለማከናወን ሶስት(3) ዋና ዋና የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነርሱም፡-

1. የአካባቢ ጥበቃ ምርምር ስራዎች (Environmental research) ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፣
2. የምርምር ሀብት አያያዝና አስተዳደር ውጤታማነት መገምገም፣
3. የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚው ተደራሽ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን መገምገም፣

የሚሉት ናቸው፡

**የኦዲቱ የመመዘኛ መስፈርት**

16. የኦዲት ቡድኑ የተለዩትን ሶስት(3) የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎችን መነሻ በማድረግ የምርምር ሥራዎችንና የምርምር ፈንድ አጠቃቀምን ለመገምገም የሚያስችሉ 32 የመመዘኛ መስፈርቶች(Evaluative criteria) ተለይቷል::/የመመዘኛ መስፈርቱ በአባሪ-3 ተመልክቷል/

**የኦዲቱ ወሰን፡-**

17.ኦዲቱ የተከናወነው በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን የኦዲት ወሰኑ ከ2009–2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት የተከናወኑ የአካባቢ ጥበቃ፣ ምርምር እና የምርምር ፈንድ አጠቃቀም ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን፣ አፈፃፀማቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማ እና አካባቢ እንክብካቤ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ሥራው በሚገኙባቸው በስድስት ዋና ዋና የምርምር መስኮች እና ከአስራ አራት የምርምር ጣቢያዎች በናሙና 4ቱን የምርምር

ጣቢያዎች በመምረጥ የተከናወነ ነው፡፡ የምርምር ጣቢያው እና ዋና ዋና የምርምር የትኩረት መስኮች ዝርዝር በአባሪ-4 ተያይዘዋል፡፡

**የኦዲቱ ዘዴ**

18. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ሲሆን መረጃው የተሰበሰበው የተለያዩ የሰነድ እና የኤሌክትሮኒክስ ቅጅ (soft copy) የቀረቡ ማስረጃዎችን በመከለስ እና የዩኒቨርሲቲውን ስድስት ዋና ዋና የምርምር ትኩረት መስኮች ለሚመሩት ቡድን መሪዎች፣ ለምርምር ኤክስቴሽንና ህትመት ዳይሬክቶሬት፣ ለማህበረሰብ ልማት ሥራዎች ዳይሬክቶሬት፣ ማዕከላዊ ቤተ ሙከራ አስተዳደር ኃላፊ፣ የማዕከል ንብረት አስተዳደር ኃላፊ፣ የሀረማያ ሀይቅ ተፋሰስ ልማት ፕሮጀክት የቴክኒክ ሥራዎች አስተባባሪ፣ የደንጋጎ ፕሮጀክት ዋና አስተባባሪ፣ እንዲሁም ከባለድርሻ አካላት የሀረማያ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት እና የተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ጽ/ቤት፣ የቀርሣ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት፣ የድሬደዋ ግብርና ቢሮ እና አካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን፣ የሀረሪ ክልል ግብርና ቢሮ፣ የባቢሌ ወረዳ ግብርና ጽ/ቤት ለስራ ሃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ እና የመስክ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡

# ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

**የምርምር ጭብጦችን በየአምስት ዓመቱ የሚለዩ መሆኑን በተመለከተ፣**

19.የዩኒቨርሲቲ የምርምር ጭብጦችን በብሔራዊ የምርምር አጀንዳ ከተለዩት ውስጥ ቅድሚያ የሚሹ ምርምሮችን በየአምስት ዓመቱ በመለየት ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡

20.የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ ቁጥር 1/2011 ዓ.ም እና በ2014 G.c/ 2006 ዓ.ም/ በዩኒቨርሲቲው የተዘጋጀው ሴኔት ሊጅስትሌሽን ዩኒቨርሲቲው ትኩረት የሚሹ ጭብጦችን በየአምስት ዓመት ወቅታዊ በማድረግ እንደየ ችግሩ ክብደት ቅድሚያ የሚሹ ችግሮችን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ችግር ፈቺ የሆነ ምርምሮችን ማከናወን እንዳለበት የተገለፀ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲው አሁን እየተሠራበት የሚገኘው የምርምር ጭብጦች በ2014 G.c/ 2006 ዓ.ም/ የተለየ ሲሆን መለየት ከነበረበት አራት ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑ ከተከለሱት ሠነዶች ለማወቅ ተችሏል፡፡

21.ስለ ሁኔታው ዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በተላከላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ የትኩረት መስኮቹ ከተለዩ ከ5 ዓመት በላይ መዘግየቱን የኦዲት ግኝቱ ያመለከተው ትክክለኛ መሆኑን ተቀብሎ በየዓመቱ የምርምር ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ከማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ውይይት በማከናወን በርካታ ሀሳቦች ከማህበረሰቡ በማሰባሰብ ቅድሚያ የሚፈልጉ ችግሮችን እየተለየ እየተሠራ እንደሚገኝ እና በቅርቡ በ2015 ዓ.ም የትኩረት መስኩን ወቅታዊ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

22.የሥራ ኃላፊዎቹ ይሄን ይበሉ እንጂ በየዓመቱ የምርምር ፍላጎት ዳሰሳ ጥናት ከማህበረሰብ ተወካዮች ጋር ውይይት ስለማከናወናቸው እና ስለተሰበሰቡት ጉዳዮች ጭብጥ የሚገልጽ ደጋፊ ማስረጃ ባለመቅረቡ መረጃዎችን በየዓመቱ እንሰበስባለን የተባለውን የሚለውን አልተቀበልንም፡፡

23.ዩኒቨርሲቲው በመመሪያው መሠረት ትኩረት የሚሹ ጭብጦችን በየአምስት ዓመት ወቅታዊ ያላደረገበት ምክንያት የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ ቁጥር 1/2011

ዓ.ም እና በ2014 G.c/ 2006 ዓ.ም/ የተዘጋጀው የዩኒቨርሲቲው የሴኔቱ ሌጅስሌሽን ላይ ትኩረት ባለማድረጉ ነው፡፡

24. በመሆኑም የዩኒቨርሲቲው የምርምር ጭብጦች በብሔራዊ የምርምር አጀንዳ ከተለዩት ውስጥ ቅድሚያ የሚሹ ምርምሮችን በመለየት በየአምስት ዓመት ወቅታዊ ያላደረገ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የሚሰራቸው ምርምሮች ትኩረት መደረግ ያለባቸው መስኮች ላይ እና አገራዊ አጀንዳ እንዲሁም ችግር ፈቺ ምርምሮች ኢንዲሰሩ ግልጽ የሆኑ አቅጣጫዎች እንዳይቀመጡና ለምርምር የሚመደቡ የመንግስት በጀት እንዲሁም በዩኒቨርሲቲው በትብብር የሚገኙ የምርምር ፈንድ አስፈላጊውና ወቅታዊ ምርምሮች እንዳይከናወኑ ይችላል፡፡

**የምርምር ስራዎች የህብረተሰቡን ፍላጎት መነሻ ያደረጉ መሆኑን በተመለከተ፡-**

25. በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ የምርምር ስራዎች የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት መነሻ ያደረጉ ችግር ፈቺ ሊሆኑ ይገባል፡፡

26. በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች የህብረተሰቡን ፍላጎት መነሻ ያደረጉ ቢኖሩም፡-

- ✓ ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ ችግር እና ፍላጎት ለመለየት በየዓመቱ የዳሰሳ ጥናት እንደሚያከናውኑ የተገለፀ ቢሆንም በሀረማያ እና ቀርሣ ወረዳዎች በ12 ቀበሌዎች ላይ የአፈር ጨዋማነት ማህበረሰቡን እያስቸገራቸው በመሆኑ ችግሩን ለመለየት ከሁለቱ ወረዳ የተሰበሰበ የዳሰሳ ጥናት መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በምስራቅ ሀረርጌ ከፍተኛ የፀረ-ተባይ ዝቃጭ ኬሚካል በውሃ እና በጫት ምርቶች ላይ መኖሩን በጥናትና ምርምር የለየ ቢሆንም፤ ኬሚካሉ በሰውና በእንሰሳት ላይ ያደረሰው ዐሉታዊ ተፅዕኖ ተገምግሞ በሌላ አማራጭ እንዲተካ ለማድረግ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት የተሠራ ሥራ ስለመኖሩ የሚያስረዳ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ✓ በውሃ እና በጫት ምርቶች ላይ የተከነወነው የምርምር ውጤት ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን በማህብረሰቡ ዘንድ ተደራሽ በማድረግ አሳሳቢነቱ ግንዛቤ ያልተፈጠረ መሆኑ ከተከለሱት የሠነድ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለማሣያ፡- በተገኘው የምርምር ውጤት መሠረት Dichlorodiphenyldichloroethylene (DDE) and Benzene Hexachloride

(BHC) የተሰኙ የፀረ ተባይ የኬሚካል ዝቃጮች ክምችት ከጫት ይልቅ በውሃ ውስጥ ተከማችተው የሚገኙ ሲሆን Heptachlor and DDT ክምችት መጠን በጫት ውስጥ ከፍ ያለ መሆኑን፤ ይህም ለካንሰር፣ ለነርቭ መዛባት፣ ለመተንፈሻ አካላት በሽታዎች እና ለሌሎች ተዛማች የጤና ችግሮች የሚያጋልጥ መሆኑን አመላክቷል፡፡

27. ስለሁኔታው ዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ ዩኒቨርሲቲው በየዓመቱ ምርምር የተከናወነባቸው አካባቢዎች እና የተገኙ ውጤቶችን ከተለያየ አካባቢ የግብርና ቢሮ ባለሙያዎች፣ በምርምር ላይ ዕውቀት ያላቸው ባለድርሻ አካላት የሚሳተፉበት እና ከማህበረሰብ የተወጣጡ አርሶ አደሮች በተገኙበት ግምገማ የሚያካሂዱ መሆኑን፣ በዚህም ላይ በየአካባቢው ያሉ ችግሮችን እንዲያቀርቡ የሚደረግ ሲሆን የአፈር ጨዋማነትን በተመለከተ በሀረማያ እና ቀርሳ ወረዳ ላይ ችግሩ ለዩኒቨርሲቲው ያልቀረበ መሆኑን፤ ሆኖም ግን በምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ ዞኖች የአፈር ጨዋማነት ችግር ያለባቸው ዋና ዋና ወረዳዎች በግብርና ቢሮዎች በኩል ተለይተው የቀረቡትን መነሻ በማድረግ ጥናት እየተካሄደ መሆኑን ለአብነትም በባቢሌ፣ ጉርሱም፣ ጎላ ኦዳ እና ደደር ወረዳዎች ላይ ምርምር የተከናወነ መሆኑን፣ የጨዋማነት ችግር ከፍተኛ ከሆነባቸው ቆላማ አካባቢዎች ጋር ሲነፃፀር ቀርሳ ቅድሚያ የሚሰጠው አለመሆኑን፣ ችግሩም ካለ እንደ ግብዓት ወስደው ምርምር የሚያደርጉ መሆኑን፣ ገልፀዋል፡፡

28. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ በየዓመቱ በሚያዘጋጀው ዓመታዊ የምርምር ቀን (Work shop) የህብረተሰቡን ችግር እና ፍላጎት የሚያሰባስቡ መሆኑን እና ለዚህም በስብሰባ ወቅት የተያዘው ቃለ-ጉባኤን ያቀረቡ ቢሆንም ቃለጉባኤው ላይ ተሳታፊዎች ያልፈረሙበት እና ከተሳታፊዎች የተነሱት ሀሳብ ያልተገለፀ በመሆኑ እንዲሁም ቀርሳ ቅድሚያ የሚሰጠው አለመሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ባለማቅረቡ የተሰጠውን ሀሳብ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

29. ዩኒቨርሲቲው የሚገኝበት የሀራማያ እና ቀርሳ ወረዳዎች ችግር ተደራሽ አለማደረጉ እንዲሁም በውሃ እና በጫት ምርት ላይ የሚገኘው ፀረ-ተባይ ኬሚካል በሰውና

በእንሰሳት ላይ ያደረሰው አሉታዊ ተፀዕኖ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች በመሆናቸው መፍትሔ ሊያስገኝ የሚችል ምርምር አለመደረጉ በሰው ጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል፡፡

**በአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ላይ ጥናትና ምርምር መደረጉን በተመለከተ**

30. ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው/በክልሉ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በጥናትና ምርምር በመለየት ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡

31. ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው/በክልሉ/ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በጥናትና ምርምር ለይቶ ምላሽ ለመስጠት በስድስት ዋና ዋና የትኩረት መስኮችና በ 22 ንዑስ የትኩረት መስኮች በ216 የምርምር ፕሮጀክቶቸን እያካሄደ ሲሆን በያዝነው በጀት ዓመት 76 ፕሮጀክቶችን አፀድቆ ወደ ሥራ የገቡ ቢሆንም፡-

**በባቢሌ ወረዳ፡-**

- ✓ አካባቢው በተፈጥሮ በአትክልትና ፍራፍሬ የሚታወቅ ቢሆንም በምርምር እገዛ በማድረግ የተሻለ ምርት እንዲያገኝ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በምስራቅ ሀረርጌ ያለው የተፈጥሮ ሀብት የዳከታ ትክል ድንጋይ፣ የባቢሌ ዝሆን፣ የቁንዱዶ ተራራ ፈረሶች እና በጋራ ሙለታ ወረዳ የልጅ እያሱ እስርቤት ለቱርስት መስብ እንዲውል ለማድረግ የተለያየ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎበት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት እያደረገ ቢሆንም እስከ አሁን ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣
- ✓ የተራቆቱ የደንጋጎ ተራራን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ዩኒቨርሲቲው ከአካባቢና የደን ልማት ኮሚሽን ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በብር 10 ሚሊዮን በ1035 ሄክታር ላይ የሞዴል ደን የማልማቱ ስራ የጀመረ ቢሆንም ከሰኔ 2014 ዓ.ም ጀምሮ እስከ ጥቅምት 30/2015 ድረስ የፕሮጀክቱ ሥራ የተቆራረጠ መሆኑ፣

በኦዲቱ ወቅት ለወረዳ ግብርና ቢሮ ባለሙያዎች ቃለመጠይቅ ቀርበው ከተሰጠው ምላሽ ለመረዳት ተችሏል፡፡

32. ስለሁኔታው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ፡-

- ✓ በድሬዳዋ ከተማ ቶሚ እርሻ ላይ ከፍተኛ የምርምር ሥራ በመሥራት የተለያዩ የአትክልት ሰብሎችን እንደ ካሮት፣ ድንች፣ ሻሎት፣ የመሳሰሉትን በማልማት ለድሬደዋ አስተዳደር፣ ለሀረሪ ክልል እና ምስራቅ ሀረርጌ ድጋፍ ያደረጉ መሆኑን፤እነዚህ የተሻሻሉ ዝርያዎች በገበሬዎች ማሰልጠኛ ማዕከል እና አርሶ አደሮች ማሳ ላይ ለማሳያ ቀርቦ በተለያዩ ወረዳዎች፣ ዞኖች እና ክልሎች ሳይቀር በስፋት የተሰራጨ መሆኑን፣
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በባቢሌ ወረዳ የባቢሌ ዝሆኖች መጠለያ ላይ እየተስተዋለ ያለውን ችግር ለመቅረፍ እና የዳከታ ትክል ድንጋይ እንዲሁም በጋራ ሙለታ ወረዳ የልጅ እያሱ እስርቤት ለቱርስት መስብ እንዲውል ከፌሎርዳ ዩኒቨርሲቲ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ጥናትና ምርምር ተከናውኖ ምላሽ እንዲያገኙ ለማድረግ ጥረት እያደረገ መሆኑ እና በተጨማሪ በተገኘው የመንግስት መድረክ ሁሉ ባለድርሻ አካላት ድጋፍ እንዲያደርጉ ሀሳብ እያቀረበ መሆኑን፣
- ✓ የተራቆቱት መሬቶችን እና ተደጋጋሚ ድርቅን በተመለከተ ዩኒቨርሲቲው በየዓመቱ ከ400 ሺህ በላይ የዛፍና ፍራፍሬ ችግኞችን በማፍላት በምስራቅ ሐረርጌ ዞን እና በሃረሪ ክልል ለሚገኙ ወረዳዎች እያከፋፈለ መሆናቸውና ከነዚህም ውስጥ 32 ሺህ ፍሬያቸው የሚበሉ ችግኞች በወረዳው የተፈጥሮ ሀብትና ግብርና ጽ/ቤቶች እንዲሰራ የተደረገ መሆኑን፣
    - ቀድመው ሊደርሱ የሚችሉ የሰብል አይነቶችን(early maturing varieties) በምርምር የለቀቀ መሆኑ፣
    - በድርቅ ለተጎዱ አካባቢዎች የአደጋ ጊዜ ዘር(emergency seeds) በስፋት ድጋፍ ያደረገ መሆኑ፣
    - ድርቅን ለመቅረፍ አስተዋፅዖ ባላቸው የተፈጥሮ ጥበቃ ስራዎች ላይ ምርምር ያደረገ መሆኑን (ለምሳሌ፡- የሐረማያ የውሃ ተፋሰስ ልማት፣ የደንጋጎ ሞዴል ፕሮጀክት) ተጠቃሽ መሆኑን፣
    - የተራቆቱ የደንጋጎ ተራራን መልሶ ማገገምን በተመለከተ የበጀት መዘገየት ችግሮች ቢያጋጥምም ዩኒቨርሲቲው ከወረዳው አጋሮች ጋር በመተባበር በተገኘው እምቅ ውጤት የቀርሳ ወረዳን እንዲያካትት ተደርጎ ተጨማሪ በጀት በ2015 ያገኙ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

33. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለፀው ምላሽ ቢሰጡም፡-

- ✓ በዋና ካምፓስ ራሬ የምርምር ጣቢያ እና በድሬደዋ ከተማ ቶሚ እርሻ ላይ ከፍተኛ የምርምር ሥራ በመሥራት ለተለያየ አካባቢዎች ተደራሽ ማድረጉን የገለፁ ቢሆንም፤ ለባቢሌ ወረዳ ለምን ተደራሽ ማድረግ እንዳልተቻሉ የተገለፀ ባለመኖሩ፣
- ✓ በባቢሌ ወረዳ የባቢሌ ዝሆኖች ላይ እየተስተዋለ ያለውን ችግር ለመቅረፍ፣ የዳከታ ትክል ድንጋይ እና የጋረ ሙለታ ወረዳ የልጅ እያሱ እስርቤት ለቱርስት መስብ እንዲውል ከፊሎሪዳ ዩኒቨርሲቲ ጋር ግንኙነት በመፍጠር ጥናትና ምርምር ተከናውኖ ምላሽ እንዲያገኙ ለማድረግ ጥረት እየተደረገ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም እስከ አሁን አፈፃፀሙ በምን ደረጃ እንደሚገኝ የተገለፀ ነገር ባለመኖሩ፣
- ✓ ድርቅን ለመቅረፍ አስተዋፅዖ ባላቸው የተፈጥሮ ጥበቃ ስራዎች ላይ ምርምር ያደረጉ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም በተጠቀሱት ቦታዎች ላይ የተሠሩ ሥራዎች ስለመኖሩ ማስረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ በተሟላ መልኩ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

34. ዩኒቨርሲቲው በአትክልትና ፍራፍሬ የምርምር ውጤቶችን ለአካባቢ፣ ለክልል እና ለአገሪቱ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ተደራሽነትን ለማሳለጥ፤ እንዲሁም በምስራቅ ሀረርጌ አካባቢ የተራቆቱ መሬቶች መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ከሚመለከታቸው የመንግስት መዋቅር (ከክልል እስከ ቀበሌ )፣ ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች እና ከባለሀብቶች ጋር በቅንጅት በመሥራት እልባት እንዲያገኝ ካልተሠራ የማህብረሰቡን ችግር ለመፍታት እና ተደራሽ ለማድረግ አዳጋች ይሆናል፡፡

**ምርምር ሥራዎች የአገር በቀል እውቀት ላይ ያተኮሩ መሆኑን በተመለከተ፡-**

35. ተመራማሪዎች በምርምርና ጥናቶቻቸው ለአገር በቀል እውቀት ላይ ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩ ይገባል፡፡

36. ዩኒቨርሲቲው በሀገር በቀል (የባህላዊ) ዕውቀት ላይ ከ2009 በጀት ዓመት ጀምሮ እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት ብር 3,249,985 ወጪ የወጣባቸው 14 ምርምሮች የተጠናቀቁ ቢሆንም የምርምር ውጤቱ ለማህበረሰቡ ተደራሽ ያልተደረገ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት የሠነድ መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለማሣያ፡- በሐረርና

አካባቢዋ 151 ለባህላዊ መድኃኒትነት የሚውሉ እፀዋትን ከተዛማጅ አገር በቀል ዕውቀቶች በጥናትና ምርምር የለዩ ቢሆንም እነዚህ ዕፀዋቶች ቁጥራቸው በመመናመን እንዲሁም ሥነ-ምህዳራዊ እና ባህላዊ ፋይዳቸው አደጋ ላይ መሆኑን በ2011 ዓ.ም በፖሊሲ መግለጫ ላይ ያመላከቱ ሲሆን ወደ ዘመናዊ መድሃኒትነት ተቀይሮ ህብረተሰቡ በተሻለ መልኩ እንዲጠቀም እና ለእፅዋቶቹ እንክብካቤ እንዲደረግ አለመደረጉ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

37. ስለ ሁኔታው ምርምርን የሚመሩ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በሀገር በቀል(የባህላዊ) ዕውቀቶች ዙሪያ በርካታ ምርምሮች ተከናውኖ ለህትመት የበቁ ቢኖርም፤ ወደ ገንዘብ ለመቀየር ለባለሀብት ለማስተዋወቅ እና ለኢንዱስትሪ ማቅረቡ ላይ ያልተሠራ በመሆኑ ለወደፊቱ ለመስራት ጥረት የሚያደርጉ መሆናቸውን አስረድቷል፡፡

38. ዩኒቨርሲቲው በሐረር አካባቢ 151 ለባህላዊ መድኃኒትነት የሚውሉ ዕፀዋቶች መኖሩን እና እነዚህም እፅዋቶች ለመጥፋት በመመናመን ደረጃ የሚገኙ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም፤ ለባለሀብት በማስተዋወቅ እፅዋቶቹ እንክብካቤ እንዲደረግላቸው እና ባህላዊ መድኃኒታቸው ወደ ዘመናዊ መድሃኒትነት እንዲቀየር ባለመደረጉ ጠቃሚ የሆኑ የአገር በቀል ዕውቀቶች እና እፀዋቶች እንክብካቤ በማጣት ከመጥፋቱም ባሻገር ሥነ-ምህዳራዊ ጠቀሜታቸው በችግር ላይ ሊወድቁ ይችላሉ፡፡

**የምርምር ሥራዎቹ የአካባቢ ብክለትን መከላከልን ያካተተ መሆኑን በተመለከተ፡-**

39. ዩኒቨርሲቲው በምርምር ሥራዎቹ ወይም በሁለገብ ሥራዎቹ ውስጥ ተገቢውን የአካባቢ ደረጃ በመተላለፍ አካባቢን ሊበክል ወይም በሌላ አካል እንዲበከል ሊያደርግ አይገባም፡፡

40. ይሁን እንጂ ከሃረማያ ዩኒቨርሲቲ፡-

- ✓ ሀረር ጤና ኮሌጅ፣ ሕይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል እና ሐርሜ (የማይጅ) ጠቅላላ ሆስፒታል የሚወጡት ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገጃ ፕላንት(Treatment plant) እና ደረቅ የሕክምና ቆሻሻዎችን ለማስወገድ የሚያስችል ምቹ ሁኔታ ያልተፈጠረ መሆኑ፣ ለማሣያ፡-

- በዓመት ከ146,516 በላይ ታማሚዎችን የሚያስተናግድ የሀረማያ ህይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻ አልፎ አልፎ ወደ ማህበረሰቡ የሚለቀቁ መሆኑ፣
- ከህይወት ፋናና ሐርሜ ሆስፒታል የሚሰበሰቡ ደረቅ ቆሻሻ ማቃጠያ ኢንስኔሬተር ባለመኖሩ በአካባቢው ላይ ጉዳት በሚያደርስ መልኩ በሆስፒታሎቹ ግቢ ውስጥ በቃጠሎ የሚወገዱ መሆኑ፣

✓ ከሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ የሚሰበሰቡ ደረቅ ቆሻሻዎች፣ ፕላስትኮች እና ካርቶኒዎች በጉድጓድ ውስጥ እየተቀበረ የሚወገድ ሲሆን ይህ ሂደት መልሶ መጠቀም(Recycle)፣ ወደ ኮምፖስት መቀየር እና በኃይል ምንጭነት ለመጠቀም የማያስችል መሆኑን፣ በመስክ ኦዲቱ ወቅት ከባለሙያ ማብራያ እና በመስክ ምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡



**ፎቶ ቁ**-1 በህይወት ፋና ስፔሻላዝ ሪፈራል ሆስፒታል ግቢ ውስጥ እየተቃጠለ ያለው የደረቅ ቆሻሻ



**ፎቶ ቁ** -2 ከህይወት ፋና ከሆስፒታል ወደ ውጪ የሚለቀቅ ፈሳሽ የሚያሣይ

41. ስለሁኔታው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በተላከላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ ፡-

- ✓ ሕይወት ፋና ኮምፕሬሄንሲቭ እስፔሻላዘድ ሪፈራል ሆስፒታል እና ሀርሜ(የማጅ) ጠቅላላ ሆስፒታል የሚወጡ ፈሳሽ እና ደረቅ ቆሻሻዎችን በተመለከተ የተባለው ችግር መኖሩን፣ ተቀብሎ ለጊዜያዊ እና ዘላቂ መፍትሔ በመስጠት እየተሠራ መሆኑን፣
- ✓ ከሆስፒታሉ የሚወጣው ደረቅ ቆሻሻ አካባቢን በማይበክል መልኩ ከከተማ ውጪ እየተወገደ መሆኑን ገልፀው ለወደ ፊት ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት የማቃጠያ (Incinerator) ግዥ ለመፈፀም በሂደት ላይ መሆናቸውን፣
- ✓ የፈሳሽ ቆሻሻ አወጋገድን በተመለከተ ለህይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል እና ለሀርሜ ሆስፒታል በጊዜያዊነት የሚያገለግል በጤና የሴፕቲክ ታንክ ቁፋሮ እየተደረገ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

42. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለፀው ምላሽ ቢሰጡም ከሆስፒታሉ የሚወጣው ፈሳሽ ወደ አካባቢ እየተለቀቀ መሆኑን እና ደረቅ ቆሻሻ አካባቢን በሚበክል መልኩ በሆስፒታሎቹ ግቢ ውስጥ ሲቃጠል በመስክ ምልከታም የተረጋገጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አያስችልም፡፡

43. ዩኒቨርሲቲው ሆስፒታሎችን በማደራጀት ለበርካታ ማህበረሰብ እየሰጠ ያለው አገልግሎት የተሻለ ቢሆንም በዚያው ልክ ከሆስፒታሎቹ የሚወጡ ፈሳሽ እና በግቢ ውስጥ የሚቃጠሉ ደረቅ የሕክምና ቆሻሻዎች በማህበረሰቡ ጤና እና በአካባቢው ላይ የሚያደርሱት አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ በመሆኑ ቶሎ እልባት ባለማግኘቱ ለህብረተሰቡም ሆነ ለአካባቢ ከፍተኛ ሥጋት ሆኗል፡፡

**የፕሮጀክቶች አፈፃፀም ላይ ክትትልና ግምገማ መደረጉን በተመለከተ፡-**

44. ዩኒቨርሲቲው ለየምርምር ፕሮጅክቶች የተመደበው በጀት በትክክል ለታለመላቸው ዓላማ መዋሉን በየጊዜው የፕሮጀክቶቹን ፊዚካል እና ፋይናንሻል አፈፃፀም ክትትልና ግምገማ በማድረግ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ሊደረግ ይገባል፡፡

45. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ 1/2011 ዓ.ም አንቀጽ 3 ላይ ዩኒቨርሲቲው አግባብነት ካላቸው የሥልጠና መስኮች ብቃት ያለው የክትትልና ግምገማ ቡድን በመቋቋም ምርምሮች በየደረጃ ማለፍ ያለባቸውን ሂደት ይመግማል የሚል ቢሆንም፤ በዩኒቨርሲቲው ይህ ቡድን ተቋቋሞው ወደ ሥራ ባለመገባቱ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓቱ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለማሣያ፡-

- የምርምር ሥራዎች በየደረጃው ያደረጉትን እድገት(ያሉበት ሂደት) ስለመገምገሙ የሚያስረዳ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በአፈጻጸም ወቅት ያሉ ችግሮችን በመለየት ለችግሮቹ መፍትሔ ስለመሰጠቱ የሚያስረዳ የክትትልና ግምገማ መረጃ ያልቀረበ መሆኑ፣
- በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች ፊዚካል እና ፋይናንሻል አፈፃፀማቸው በየሩብ ዓመት እና በየስድስት ወሩ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ አፈፃፀማቸው ተገምግሞ ግብረ-መልስ የማይሰጥ መሆኑ፣
- ከመንግስት ለምርምር ከሚመደበው መደበኛ በጀት ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት በየ2 ዓመት መጠናቀቅ ከነበረባቸው የምርምር ፕሮጀክቶች ዝርዝር ውስጥ ብር 12,664,269.75 የተመደበላቸው 69 ፕሮጀክቶች ከ1 እስከ 4 ዓመት የተጓተቱ መሆኑ፣
- ከ2009 እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት በውጭ የገንዘብ ድጋፍ 49,534,083.80 USD፣ Nok 989,000 እና ብር 2,799,204.54 የተከናወኑ 68 የምርምር ፕሮጀክቶች የተጠናቀቁ፤ በብር 54,940,159 እየተከናወነ የሚገኙ 41 የምርምር ፕሮጀክቶች የምርምር ውጤት እና ሂደት አፈፃፀማቸው ምርምሩን ለሚመሩት የሥራ ክፍሎች ቀርቦ የማይገመገሙ መሆኑ፣
- ከምርምር የሥራ ክፍል በቀረበው መረጃ መሠረት ከ2009 እስከ 2014 በጀት ዓመት መጨረሻ ከግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት ለምርምር ሥራ የተገኘው የገንዘብ ድጋፍ ብር 16,955,102.07 ቢኖርም የምርምር ፕሮጀክቶች፡-
  - በዩኒቨርሲቲው የፕሮጀክት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ተመዝግቦ አፈፃፀማቸው ክትትልና ቁጥጥር የማይደረግበት መሆኑ፣

- የፋይናንሻል አፈፃፀማቸው የ2009፣ 2010 እና 2011 በጀት ዓመታት ከ3 ዓመት ቆይታ በኃላ በ2012 ዓ.ም ለግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት የቀረበ ሲሆን ከ2012 በጀት ዓመት እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት ሪፖርት ያልቀረበ መሆኑ፣
- ከኢንስቲትዩቱ የሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ በዩኒቨርሲቲው የሂሳብ አካውንት ገቢ በማድረግ ምርምሩን በሚመሩት የበላይ ኃላፊዎች እየፀደቀ ወጪ የሚደረግ ቢሆንም የፊዚካል እና የሂሳብ ሪፖርት ተዘጋጅቶ አፈፃፀማቸው የማይገመገም መሆኑ፣
- ከ2009 እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት ምን ያህል ምርምሮች ከኢንስቲትዩቱ በተገኘ የገንዘብ ድጋፍ እንደተከናወኑ በምርምር የሥራ ክፍሎች ዝርዝር መረጃ ያልተገኘ መሆኑ፣
- በተገኘው የገንዘብ ድጋፍ የምርምር ውጤቱ ለማህበረሰቡ ያስገኘው ተጨባጭ ለውጥ ስለመኖሩ የሚያሣይ መረጃ በዩኒቨርሲቲው ያልቀረበ መሆኑ፣ ከተከለሱት መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡

46. ስለሁኔታው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና የነባራዊ ሁኔታ መግለጫና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ላይ በሰጡት ምላሽ ፡-

- ✓ ዩኒቨርሲቲው በቅርቡ የክትትልና ግምገማ መመሪያዎችን አጽድቆ ተግባራዊ ማድረግ የጀመረ በመሆኑ ሁሉም ተመራማሪዎች ቢያንስ በዓመት ሦስት ጊዜ የሂደት ሪፖርት እና ዓመታዊ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ ክትትልና ግምገማ የሚደረግ መሆኑን ገለፀው  ሆኖም ግን አንዳንድ ፕሮጀክቶች በሰዓቱ የማይጠናቀቁበት ምክንያት በኬሚካል እና ሌሎች የምርምር ግብዓቶች በወቅቱ አለመገኘት(በግዥ ሥርዓቱ ቢሮክራሲ ምክንያት) የጊዜ ገደብ ውስጥ ያልተጠናቀቁ ቢኖርም አብዛኞቹ ፕሮጀክቶች በኮቪድ-19 ምክንያት ከአንድ ዓመት በላይ የዘገየ መሆኑን፣
- ✓ የPHD ተማሪዎች የሚከናወኑ ምርምሮች ተጫማሪ ጊዜ በመውሰዳቸው መዘገየት የቻለ መሆኑን፣
- ✓ በውጭ የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ ምርምሮችን በተመለከተ የፊዚካልና ፋይናንሻል አፈፃፀም ሪፖርት ገንዘቡን ድጋፍ ለሚያደርገው አካላት ብቻ

የሚያቀርቡ መሆኑን፤ ለወደፊቱ ግን ለምርምር የሥራ ክፍሉ ተጠሪ የሆነ አዲስ እየተዘጋጀ ባለው የዩኒቨርሲቲው አደረጃጀት ውስጥ በመዋቅር ደረጃ እንዲካተት በማድረግ ከውጭ ድርጅቶች በሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶችን የሚያስተዳድር የሥራ ክፍል እንዲኖር በማድረግ አፈፃፀማቸው በየሩብ ዓመት፣ በየስድስት ወሩ እና በየዓመቱ እንድገመገሙ ለማድረግ የታሰበ መሆኑን እስከ አሁን ባለው በውል ስምምነቱ መሠረት ፊዝካል እና ፋይናንሻል አፈፃፀም ባለድርሻ አካላትን በማሳተፍ በመገምገም እና ሂሳባቸውም በውጪ ኦዲት ጭምር ኦዲት የሚደረግ መሆኑን፣

- ✓ ከግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች በዩኒቨርሲቲው እና የኢኒስቲትዩቱ ባለሙያዎች ቀጥታ ግንኙነት በመፍጠር ሲሠሩ ስለነበረ ተመራማሪዎች የፊዝካል ሥራውን እና የፋይናንሻል ሪፖርቱን እንዲያቀርቡ በማድረግ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ለማከናወን ያልተቻለ መሆኑን፣
- ✓ የሂሳብ ሪፖርት በ2012 በጀት ዓመት በዩኒቨርሲቲው ተሠርተው ሪፖርት እንዲደረግላቸው የተደረገው ኢንስቲትዩቱ ድጋፍ ላደረገው አካል የፋይናንሻል ሪፖርት እንዲቀርብላቸው በመፈለጉ መሆኑን፣
- ✓ በተጨማሪ ኢኒስቲትዩቱ በዩኒቨርሲተው ምርምር ጽ/ቤት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት እንዲኖረው በማድረግ የሚሰሩ ምርምሮችን ክትትልና ግምገማ ለማድረግ መግባባት ላይ የደረሱ መሆኑን፤ ገልጸዋል፡፡

47.የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለፀው ምላሽ ቢሰጡም፡-

- ✓ ዩኒቨርሲቲው በቅርቡ የክትትልና ግምገማ መመሪያዎችን አጽድቆ በየሩብ ዓመቱ፣ በየስድስት ወሩና በየዓመቱ ሪፖርት እንዲያቀርቡ እየተደረገ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም ሪፖርት ቀርቦ ተገምግሞ ግብረመልስ ስለመሰጠቱ የሚያስረዳ መረጃ ያልቀረበ በመሆኑ፣
- ✓ በውጭ የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ ምርምሮችን በተመለከተ የፊዝካልና ፋይናንሻል አፈፃፀም ሪፖርት ገንዘቡን ድጋፍ ለሚያደርገው አካላት ብቻ የሚያቀርቡ መሆኑን የገለፁ ቢሆንም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ ቁጥር 1/2011 ዓ.ም አንቀጽ 16 የምርምር ፈንድን ስለማስተዳደር በሚል ስር

በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው የዩኒቨርሲቲው ምክትል ፕሬዘዳንት የከፍተኛ ትምህርት ተቋሙን የምርምር ፈንድንና ድጋፍ ያስተዳደራል፤ በየዓመቱም አፈፃፀማቸውን ያሳውቃል የሚል በመሆኑ፣ የተሰጡትን ምላሾች ለመቀበል አልተቻለም፡፡

48. ዩኒቨርሲቲው መዋቅራዊ አደረጃጀቱን በጠበቀ መልኩ የምርምር ሂደት ፊዝካል እና ፋይናንሻል አፈፃፀም ሪፖርት በየጊዜው ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ በማድረግ ክትትልና ግምገማ ባለመከናወኑ ከተለያየ ምንጭ ተገኝተው የተመደበው በጀት በትክክል ለታለመላቸው ዓላማ መዋሉን አጠራጣሪ ከማድረጉም በላይ የምርምር ውጤቱ ጥራት ያልጠበቀ፣ የታለመለት ዓላማ የማያሣካ እና በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዳይጠናቀቁ ብሎም በአንዳንድ ፕሮጀክቶች ላይ እንዲቋረጡ ክፍተት ፈጥሯል፡፡

**ለምርምር ስራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እየቀረበ መሆኑን ተመለከተ:-**

49. ዩኒቨርሲቲው ለምርምር ስራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በወቅቱ ሊያሟላ ይገባል፡፡

50. በዩኒቨርሲቲው ለምርምር ሥራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ለማግኘት የግዥ ሂደቱ ከአንድ ዓመት በላይ የሚጓተቱና በወቅቱ የማይቀርብ በመሆኑ ተመራማሪዎች ለምርምር ያላቸው ፍላጎት እየቀነሰ የመጣ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለማሣያ፡- ለመሠረታዊ ሣይንስ የምርምር ትኩረት መስክ በ2014 በጀት ዓመት የምርምር ገንዘብ ድጋፍ ለማግኘት ያመለከቱት አመልካቾች ብዛት 25 ሲሆን ለ2015 በጀት ዓመት ያመለከቱት ብዛት 11 ብቻ በመሆኑ ከግማሽ በላይ እንዲቀንስ ያደረገው በግብዓት አቅርቦት እጥረት መሆኑ ታውቋል፡፡

51. ስለሁኔታው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በተላከላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ በግዥ ሂደቱ ላይ በኦዲት ግኝቱ የተነሱት ነጥቦች ትክክለኛ መሆናቸው ተቀብሎ ችግሩ ግን በፌዴራል ግዥ ሂደት ኅታችነት መሆኑን፤ ከዚህም በተጨማሪ እንደኬሚካል ያሉ የላብራቶሪ ፍጆታዎች በአገር ውስጥ ገበያ በቀላሉ የማይገኙ ግብዓቶች በመሆናቸው ፕሮጀክቶች አዋርድ ከተደረገ (ከተሰጠ) በኃላ የምርምር ግብዓቶች ዋጋ በከፍተኛ የሚጨምር በመሆኑ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

52. ዩኒቨርሲቲው ለምርምር ሥራ የሚያስፈልገው ግብዓት በወቅቱ ባለማቅረቡ የምርምር ሂደቱን እንዲዘገይ ከማድረጉም በላይ ምርምሩ እንዲቋረጥ በማድረግ በተመራማሪዎች ተነሳሽነት ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ በማሳደር ከምርምር እንዲርቁ ሊያደርግ ችሏል፡፡

**ኮንትራት በሚገቡ ተመራማሪዎች ላይ ክትትልና ቁጥጥር መደረጉን በተመለከተ፡-**

53. በዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥራ ለማከናወን ኮንትራት የሚገቡት ተመራማሪዎች አስቀድሞ በወሰዱት ኮንትራት ላይ ውጤታማ መሆናቸውን ከተረጋገጠ በኋላ ሌላ የምርምር ኮንትራት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡

54. ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥራ የሚያከናውኑ ተመራማሪዎች አስቀድሞ የወሰዱትን የምርምር ኮንትራት ሣያጠናቅቁ ተጨማሪ ኮንትራት የሚሠጣቸው መሆኑን ከተከለሱት የምርምር ዝርዝር መረጃ ለመረዳት ተችሏል፡፡ ለማሣያ፡- እያንዳንዱ የምርምር ፕሮጀክት በየ2 ዓመት የሚጠናቀቁ ሲሆን አንድ ተመራማሪ ከአንድ የምርምር ፕሮጀክት ላይ ብቻ ዋና ተመራማሪ ሆኖ መሥራት እንደሚችል መረጃዎች የሚያስረዱ ቢሆንም ከ2009 እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመታት በየ2 ዓመታት ጊዜው ውስጥ ከ3 እስከ 7 ዋና ተመራማሪዎች መኖራቸው ተውቋል፡፡

55. ስለ ሁኔታው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች የማጠቃለያ ጥያቄ እና በተላከላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በፁሑፍ በሰጡት ምላሽ በዩኒቨርሲቲው አሠራር አንድ ተመራማሪ በዓመት በሶስት የምርምር ፕሮጀክቶች ውስጥ መሳተፍ የሚችል መሆኑን ይህም በአንዱ እንደ መሪ ተመራማሪ እና በሁለት ተባባሪ ተመራማሪ በመሆን ብቻ መሳተፍ እንደሚችል ገልጸዋል፡፡

56. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ዋና ተመራማሪ በአንድ ዓመት በአንድ ዋና ተመራማሪ እና በሁለት ተባባሪ ተመራማሪ በመሆን ብቻ መሳተፍ እንደሚችሉ የገለፁ ቢሆንም የምርምር ፕሮጀክት በየ2 ዓመት የሚጠናቀቁ በመሆኑ በየሁለት ዓመታት ጊዜው ውስጥ ከ3 እስከ 7 ተመራማሪ ሆኖ የሚሣተፉ መኖሩን መረጃዎች የሚያስረዱ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

57. በመሆኑም በዩኒቨርሲቲው ለምርምር ኮንትራት የሚገቡት ተመራማሪዎች አስቀድሞ የወሰዱት የምርምር ፕሮጀክቶች ላይ ውጤታማ መሆናቸው እየተረጋገጠ ባለመሰጠቱ በተመራማሪ ላይ የሥራ ጫና በመፍጠር የምርምር ፕሮጀክቶቹ በታሰበው ወይም በተገባው የኮንትራት ጊዜ ውስጥ እንዳይጠናቀቁ እና ጥራታቸው አጠያያቂ እንዲሆን

የሚያደርግ ከመሆኑም በላይ የምርምር በጀት ለታሰበው አላማ እንዳይውል ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የምርምር ውጤት ርክከብ ማድረጋቸውን በተመለከተ፣**

58. የዩኒቨርሲቲው የምርምር ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲው ሲለቁ የደረሱበትን የምርምር ውጤት፣ የፋይናንስ ሪፖርት እና ቴክኒካል ውጤቶች ርክክብ የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

59. ይሁን እንጂ በዩኒቨርሲቲው የምርምር ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲው ሲለቁ የደረሱበትን የምርምር ውጤት፣ የፋይናንስ ሪፖርት እና ቴክኒካል ውጤቶች ርክክብ የሚደረግበት ስርዓት ቢኖርም አልፎ አልፎ ርክክብ ሳያደረጉ የሚለቁበት ሁኔታዎች መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰቡ ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለማሣያ፡- ከ2009 እስከ 2014 በጀት ዓመት በብር 3,80,473.88 በጀት ተመድቦላቸው የምርምር ሥራ የተጀመሩ 21 ፕሮጀክቶች በባለሙያ መልቀቅ የተቋረጡ መሆኑ፣ ለእነዚህ ለተቋረጡት ፕሮጀክቶች ተመደበለት በጀት የተገለፀ ቢሆንም ከወጪ ጋር ተነፃፅሮ ባለመቅረቡ ምን ያህል ክፍያ እንደተፈፀመ የሚያሳይ መረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣

60. ስለሁኔታው ምርምር የሚመሩ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ አንዳንድ ተመራማሪዎች ክሊራንስ ሳይጠይቁ የደረሱበትን የምርምር ውጤት ፊዝካል እና ፋይናንሻል ሪፖርት ሳያስገቡ እና ርክክብ ሳያደርጉ በመሄዳቸው ምክንያት መሆኑን እና የወጣው ወጪ ከዩኒቨርሲቲው ፋይናንስ ዳይሬክቶሬት ማግኘት የሚቻል መሆኑን አስረድቷል፡፡

61. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለፀው ምላሽ ቢሰጡም የዩኒቨርሲቲው የምርምር የኮንትራት ስምምነት ተመራማሪዎች በወሰዱት ኮንትራት በውል ስምምነቱ መሠረት በተናጠል እና በቡድን ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታዎች ያለ ሲሆን ዋና ተመራማሪ ሥራውን አቋርጠው በሚሄድበት ጊዜ ግማሽ ፐርሰንት ተባባሪ ተመራማሪዎች ተጠያቂ የሚሆኑበት ሁኔታዎች በመኖሩ ይህ ተግባራዊ መደረጉን የሚያስረዳ መረጃ ያልቀረበ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

62. በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የምርምር ባለሙያዎች/ተመራማሪዎች/ በተለያየ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲው ሲለቁ የደረሱበትን የምርምር ውጤት፣ የፋይናንስ ሪፖርት እና ቴክኒካል

ውጤቶች በውል ስምምነቱ መሠረት ርክክብ ሳይፈፀሙ በሚሄዱት ላይ ተጠያቂነትን ተግባራዊ ባለማድረጉ ተመራማሪዎች ኮንትራት ከፈረሙ በኃላ በግዴለሽነት አቋርጠው በመሄዳቸው የመንግስት ገንዘብም ለብክነት እንዲዳረግ ምክንያት ሆኗል ፡፡

**የምርምር ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ ሥርዓት መዘርጋትን በተመለከተ፡-**

63. ዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ ሥርዓትን በመዘርጋት የምርምር ጥናት ኩረጃን(Plagiarism Checker software) እና አንድ የምርምር ሥነ-ምግባር ቦርድ በመቋቋም ምርምሮች የሥነ-ምግባር መርህን ተከትለው እንዲሰሩ ሊደረግ ይገባል፡፡

64. ዩኒቨርሲቲው የምርምር ጥናት ኩረጃን ለመከላከል የሚያስችል ሶፍትዌር(Plagiarism Checker software) አለመዘጋጀቱ እና የምርምር አጀንዳዎች ድግግሞሽ እንዳይኖር ምርምር ከመጀመሩ በፊት ከሌላ የምርምር ተቋማት ጋር የተመረጡ አጀንዳዎች በጋራ የሚገመገሙበት ሥርዓት የሌለ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

65. ስለሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው ምርምር የሚመሩ የሥራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ችግር መኖሩን በመገምገም ሶፍትዌሩን(Plagiarism Checker software) ለመግዛት በዕቅድ ይዞ የነበረ ቢሆንም የትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለየብቻ ከሚገዙ በአንድነት ተቀናጅቶ ቢገዙ ይሻላል የሚል አቅጣጫ ይዞ ስለነበረ እስከ አሁን ግዥ መፈፀም ያልቻሉ መሆኑን እና በአሁን ወቅት ግን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ጋር ግዥው ተከናውኖ ወደ ሥራ ለመግባት በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣
- ✓ የምርምር አጀንዳዎች ድግግሞሽ እንዳይኖር ምርምር ከመጀመሩ በፊት ከተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሚት ጋር በጋራ ግምገማ ለማድረግ ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቅ በመሆኑ ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስቸግር መሆኑን፣

ገልጸዋል፡፡

66. በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ ሥርዓትን በመዘርጋት የምርምር ጥናት ኩረጃን(Plagiarism Checker software) እና የምርምር ሥነ-ምግባር ቦርድ በመቋቋም ምርምሮች የሥነ-ምግባር መርህን ተከትለው እንዲሰሩ ባለመድረጉ፣

የሚወጡት ምርምሮች የተመራማሪዎች ሥራ ውጤት ስለመሆኑ የሚለይበት ሥርዓት እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡

**የምርምር ውጤቶች የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ስርዓትን በተመለከተ፡-**

67. በዩኒቨርሲቲው የተደራጀ የምርምር ውጤቶች የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

68. በዩኒቨርሲቲው የተጠናቀቁ ምርምሮችን ከነታሪካቸው ለመያዝ የሚያግዝ የተደራጀ የምርምር ውጤቶች የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፤ ለማሣያ ከ2009 እስከ 2015 1ኛ ሩብ በጀት ዓመት በስድስቱ የምርምር ትኩረት መስኮች ምን ያህል ምርምሮች ለህትመት ብቁ እንደተደረጉ የሚያስረዳ መረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ለመረዳት ተችሏል፡፡

69. ስለሁኔታው ጉዳዩ የሚመለከታቸው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በፁሑፍ በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ በአሁኑ ጊዜ የዩኒቨርሲተው ተመራማሪዎች በየዓመቱ ከ1000 በላይ የምርምር ወረቀቶችን(Articles) በታዋቂ ምርምር ጆርናሎች የሚያሳትም መሆኑን፣
- ✓ ተመራማሪዎች ምርምሩን ከጨረሱ በኃላ ቶሎ አስመዝግቦ ለማሳተም የፖሊሲ ማብራሪያ እና በተለያየ ሂደት ማለፍ ስለሚያስፈልግ አስገዳጅ ማድረግ ያልተቻለ መሆኑን፣
- ✓ የምዝገባ ሥራው እንደ ዩኒቨርሲቲ የታተሙትን እንጂ በመደበኛ በጀት፣ በውጭ የገንዘብ ድጋፍ እየተባለ ተለይተው የተመዘገበ መረጃ አለመኖሩ፣
- ✓ በየዓመቱ እንደ ዩኒቨርሲቲ ምን ያህል የምርምር ህትመቶች መታተም እንዳለባቸው በዕቀድ በመያዝ በርካታ ህትመቶች የሚታተሙ መሆኑን፣

ገልጸዋል፡፡

70. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለፀው ምላሽ ቢሰጡም በስድስቱ የምርምር የትኩረት መስኮች ምን ያህል ከመንግስት እና ከተለያየ ድጋፍ ሰጭ አካላት በተገኘው ሀብት የተከናወኑ እና እየተከናወነ የሚገኙ ምርምሮች ከነታሪካቸው ተመዝግቦ ምን

ያህሉ ምርምሮች ታትሞ ለመረጃ ተጠቃሚ አካላት ተደራሽ እንደተደረገ ለማወቅ ያላስቻለ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

71.በመሆኑም ዩኒቨርሲቲው የተደራጀ የምርምር ውጤቶች የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ስርዓት ዘርግቶ በየጊዜው ወቅታዊ በማድረግ በሀገር ሀብት እና ከሌላ ሀገር የገንዘብ ድጋፍ ተመድቦላቸው የተከናወኑ ምርምሮች ምን ያህሉ ታትሞ ለመረጃ ለማህበረሰብ ተደራሽ እንደተደረገ ባለመገምገሙ ምርምሮች ለተፈለገው ዓላማ እየዋሉ ስለመሆኑ ለማወቅ አስቸጋሪ አድርጓል፡፡

**ዘመናዊ የቤተሙከራ መደራጀቱን በተመለከተ፡-**

72.ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የምርምር ስራዎችን ለመስራት የሚያግዙ ላብራቶሪዎችን ማደራጀትና ማዘመን አለበት፡፡

73.ይሁን እንጂ አሁን በዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የምርምር ስራዎችን ለማከናወን የሚያግዙ ቤተሙከራዎች፡-

- ✓ ባለሙያዎች ከሥራ ገበታቸው ሲቀያየሩ ሲጠቀሙበት የነበረው የቤተሙከራ ንብረት ርክክብ እየተደረገ ስለመሆኑ መረጃ ተጠይቆ ያልቀረበ መሆኑ፣
- ✓ በዩኒቨርሲቲው ከ100 በላይ ቤተሙከራ ያለው ቢሆንም፤ በየጊዜው ወቅታዊ (Calibration) የማይደረጉ መሆኑ፣
- ✓ በኬሚስትሪ ቤተ ሙከራ ከ15 ዓመት በፊት የውስጥ ክፍሉን አደረጃጀት ለማስተካከል የተጀመሩ እስከ አሁን በሮች ተገጥሞላቸው ያልተጠናቀቁ መሆኑ፣ በክፍሉ ያሉ የቤተሙከራ መሣሪያ በአብዛኛው አገልገሎት የማይሰጡ አንዳንዶቹ ደግሞ አገልግሎት የሚሰጡ ሆኖ በጣም የቆሸሹና ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆኑ፣
- ✓ የምግብ ሣይንስ የቤተሙከራ አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶች የተከማቹበት፣ ክፍሉ የንብረት ማከማቻ እንጂ የቤተሙከራ የማይመስል መሆኑ፣ ባለሙያዎች የደህንነት መከላከያ ልብስ(Safety clothes) ሣይኖራቸው እንደ ቢሮ ማንኛውም ባለሙያ ያለጥንቃቄ የሚገባበት መሆኑ፣
- ✓ የፊዝክስ ዲፓርትመንት ከዘመኑ ጋር የማይሄዱ ረዥም ዕድሜ ያስቆጠሩ አሮጌ መሣሪያዎች ያሉበት መሆኑ፣ የትምህርት ካርኩለም በመቀየሩ ያለው የቤተሙከራ መሣሪያ የምርምሩን ሂደት ለማጠናቀቅ የማያስችሉ መሆኑ፣

- ✓ ከቤተ-ሙከራ የሚወጡ ፈሳሽ ነገሮች እንዴት እንደሚወገዱ የሚያሣይ ካርታ (Map) የሌለ መሆኑ፣
- ✓ በዩኒቨርሲቲው የቤተ-ሙከራ ንብረቶችን(Laboratory Work shop) የሚጠግን አደረጃጀት የሌለ መሆኑ፣
- ✓ የዩኒቨርሲተው ቤተሙከራ ለማሻሻል Haramaya university's Teaching Action for the improvements በ2021G.c እና Guideline for Laboratory Analytical Service Provision at Haramaya University February 2022 በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም ፀድቆ ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣

74.በተለያየ ቤተሙከራ ከ7 እስከ 15 ዓመታት በላይ ያለአገልግሎት የተቀመጡ የቤተ ሙከራ መሣሪያ ብዛት፡-

- ከሚፈለገው በላይ በትርፍነት በቁጥር 211 ሲሆኑ መነሻ ዋጋቸው በድምሩ ብር 30,093,526.76 መሆኑ፣
- ተበላሽቶ ጥገና የሚፈልጉ ንብረቶች ብዛት 216 በብር 28,936,606.32 መኖሩ፣
- ተከላ ያልተከናወነላቸው አገልግሎት መስጠት ያልጀመሩ ብዛት 10 ሲሆኑ የገንዘብ መጠናቸው ብር 2,073,198.1 መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ማስረጃዎች እና ከሚመለከታቸው ሥራ ኃላፊዎች ጋር በተደረገ ቃለ-መጠይቅ ለማወቅ ተችሏል፡፡

75.ስለ ሁኔታው የቤተሙከራ ኃላፊ ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ በኦዲቱ የተጠቀሱት ችግሮች ትክክለኛ መሆኑን ተቀብሎ ትልቁ ችግር በዩኒቨርሲቲ በቤተሙከራ የትምህርት ዘርፍ የሰለጠነ ባለሙያ አለመኖር እና ለማሰልጠን ዕድሉ አነስተኛ መሆኑን፣

76.በተጨማሪም የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና በተላከላቸው የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ በፁሑፍ በሰጡት ምላሽ ዩኒቨርሲቲው ካሉት ዘመናዊ እና ደረጃቸውን የጠበቁ 20 ቤተሙከራዎች ተለይተው የብቃት ማረጋገጫ እንዲያገኙ መጠነ ሰፊ ሥራዎች እየተሠራ መሆኑን፤ ዕቃዎቹ አገልግሎት የሚሰጡና እየሰጡ ያሉ ስለሆኑ የተጠቀሱት መሣሪያዎች ለሌላቸው ቤተሙከራዎች አገልግሎት እንዲውል የተገዙ መሆናቸው እንጂ ትርፍ አለመሆኑን፣ የተጠቀሱት መመሪያዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ፀድቆ ሥራ ላይ የሚውሉ መሆኑን እና በተጠቀሱት ክፍተቶች ላይ ተጨማሪ

ጥናቶች ተካሂደው የዩኒቨርሲቲው የቤተ ሙከራ ማሻሻያ ዕቅድ አካል ሆኖ ተግባራዊ የሚደረግ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

77. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በሰጡት ምላሽ ዕቃዎቹ አገልግሎት የሚሰጡና እየሰጡ ያሉ ስለሆኑ የተጠቀሱት መሣሪያዎች ለሌላቸው ቤተሙከራዎች አገልግሎት እንዲውል የተገዙ መሆናቸው እንጂ ትርፍ አለመሆኑን የገለጹ ቢሆንም የቤተሙከራ መሣሪያ ለሌላቸው የሥራ ክፍሎች የተገዛ ከሆነ ለምን በሌሎች ቤተሙከራ በትርፍነት ተገኝቶ እንደተመዘገበ ግልጽ የሆነ መብራሪያ ያልተሰጠ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል አልተቻለም፡፡

78. በመሆኑም በዩኒቨርሲቲው በተወሰኑ ዘርፍ ዘመናዊና የተደራጀ ቤተ-ሙከራ እና የቤተ-ሙከራ አስተዳደር ሥርዓት ባለመኖሩ ብር 61,103,331.18 የሚያወጣ የላቦራቶሪ መሳሪያዎች ለተገዙት ዓላማ ሳይውሉ ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ አድርጓል፡፡

**ዩኒቨርሲቲው የሐራማያ ሐይቅ ደህንነት ለመጠበቅ መስራቱን በተመለከተ፡-**

79. ዩኒቨርሲቲው የሐራማያ ሐይቅ የመጠበቅና የማስቀጠል ሥራዎች ከአካባቢው ማህበረሰብና ከከተማ አስተዳደር ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር የሐይቁን ህልውና ሊያስቀጥል ይገባል፡፡

80. ይሁን እንጂ ዩኒቨርሲቲው በሀረማያ ሀይቅ ዙሪያ የሚደረጉ የመስኖ ውሃ አጠቃቀሞች የሀይቁን ደህንነት፣ የአፈርንና የእጽዋትን ዕርጥበት መሰረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በጥናትና ምርምር ላይ ያመላከቱ ቢሆንም ከሀረማያ ከተማ አስተዳደር እና ከወረዳ አስተዳደር ጋር ጥብቅ ግንኙነት በመፍጠር የምርምር ውጤቱ በሀይቁ ደህንነት ላይ ለውጥ እንዲያመጣ የተሠራ ሥራ ስለመኖሩ የሚያስረዳ መረጃ በኦዲቱ ወቅት ያልቀረበ መሆኑ ታውቋል፡፡ ለማሣያ፡-

- ✓ ማህበረሰቡ ከ26 ሺ በላይ የውሃ ጉድጓድ በመቆፈር እና በቀን ከ4000 በላይ ሞተር ፓንፕ በመጠቀም የሀይቁን ደህንነት በሚጎዳ መልኩ እየተጠቀሙ መሆኑ፣
- ✓ ከሀረማያ ከተማ አስተዳደር የሚሰበሰቡ ደረቅ ቆሻሻዎች፣ የማይበሰብሱ ሀይላንዶችና ፕላስኮች በሀይቁ ደርቻ ላይ የሚጠራቀሙ እና በንፋስና በጎርፍ ወደ ሀይቁ የሚገቡ መሆኑ፣

- ✓ ከሀረማያ ከተማ የሚወጡ ፈሳሽ ቆሻሻዎች ቀጥታ ወደ ሀይቁ እየተለቀቀ የሚገኝ መሆኑ፣
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በዳሞታ፣ በጥንቄ እና በበጨቄ ቀበሌዎች በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የተፋሰስ ልማት ለማከናወን ጥረት ያደረገ ቢሆንም በገንደ ሰም፣ ዳሞታ(ገንደ አሊ፣ ገንደ ሮባ)፣ ጥንቄ (ገንደ በሶ፣ ገንደ ሮባ)፣ በበጨቄ(ኩሮ)፣ በቱጂ ገቢሣ(ሀራ ጂቱ)፣ በኢፋ ባቲ (ጎቤ ሠላማ)፣ በቁሬንሳ(ሀሙማ) በመሳሰሉት ቦታዎች ከፍተኛ የመሬት መቦርቦር በመኖሩ፤ አሸዋ፣ አፈር እና ደረቅ ቆሻሻ ወደ ሀይቁ እየጨመረ በደለል እንዲሞላ በማድረግ በሐይቁ ደህንነት ላይ ሥጋት እየፈጠረ መሆኑ፣
- ✓ አደሌ፣ ጥንቄ እና ሀረማያ ሦስቱ በአንድነት የሀረማያ ሀይቅ ተብሎ የሚጠሩ ሲሆን በሦስቱም ሀይቆች ዳርቻ መታረስ የሌለባቸው የሀይቁ አካል የሆኑ ረግራጋማ መሬቶች (Buffer Zone/ በከፍተኛ ደረጃ ለእርሻ እየዋለ የሚገኝ መሆኑ፣ ለምሣሌ፡-
    - በሀረማያ ሀይቅ ዙሪያ ቱጂ ገቢሣ ቀበሌ ቦዴ እና ሀጂ፣ ሀረማያ ከተማ ገንደ ቱሮ እና ገንደ ተሬ 01 ቀበሌ ፣
    - ጥንቄ ሀይቅ ዙሪያ በቱጂ ገቢሳ ቀበሌ ጎዴ፣ በኩሮ ቀበሌ እስከ ፍንቅሌ ያለው እና በቁሬንሳ ዙሪያውን፣
    - አዳሌ ሐይቅ በቢፊቱ ገዳ ቀበሌ፡- ኢፋ ኦሮሚያ፣ አደሌ ከተማ እና ደንገጎ የመሳሰሉት፣አካባቢዎች በከፍተኛ ሁኔታ እየታረሰ የሚገኙ መሆኑን የሚጠቀሱ ናቸው፡፡



**ፎቶ ቁ. 3** ከሀረማያ ከተማ በቱቦ ወደ ሀረማያ ሀይቅ እየተለቀቀ የሚገኙ ፈሳሽ ቆሻሻ



**ፎቶ ቁ.- 4** ከሀረማያ ከተማ ወደ ሀይቁ ዳር የተጣለ ደረቅ ቆሻሻ

81. ስለሁኔታው የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች በማጠቃለያ ጥያቄ እና የነባራዊ ሁኔታ መግለጫ እና ለቀረበው ረቂቅ ሪፖርት ላይ በፁሑፍ በሰጡት ምላሽ፡-

- ✓ የሀረማያ ሀይቅ ውሃን በቁጠባ መጠቀምን በተመለከተ በተለያየ ጊዜያት በሐይቁ ዙሪያ የሰፈሩ ማህበረሰብ ተወካዮችን በመሰብሰብ የግንዛቤ ማስጨበጫ ውይይቶችን ያከናወኑ መሆኑን፣
- ✓ ውስን የውሃ ሀብትን ከመጠቀም አንፃር የተለያየ ኮሚቴዎች ተዋቅሮ በተለያየ ምክንያት ወደ ሥራ መግባት ያልቻሉ መሆኑን፣
- ✓ የማይበሰብሱ ፕላስቲክ የውሃ መያዣ፣ ፈሳሽ ቆሻሻዎችን በተመለከተ በተለያየ ጊዜ የአካባቢውን እና የዩኒቨርሲቲውን ማህበረሰብ በማስተባበር የጽዳት ዘመቻ ሥራዎች የተደረገ ሆኖ በዘላቂነት ለመፍታት ስራ ፈላጊ ወጣቶችን በማህበር በማደራጀት፣ በማሰልጠን እና አስፈላጊ የቁሳቁስ ድጋፍ በማድረግ ሥራውን እንዲጀምሩ የተደረገ መሆኑን፣
- ✓ ለተቋቋመ ማህበራት የፕላስቲክ መጨፍለቂያ ቦታና ማሽን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል የተመቻቸላቸው መሆኑን፣
- ✓ ሥራውን ለማቀላጠፍ እና ምቹ ለማድረግ የቆሻሻ መጓጓዣ ትራክተሮች ግዥ በሂደት ላይ የሚገኝ መሆኑን፣

ገልፀዋል፡፡

82. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ በዝርዝር የተጠቀሱትን ጥራት እያደረጉ እንደሆነ ምላሽ ቢሰጡም፣ ማህበረሰቡ በሀይቁ ውሃ አጠቃቀም ላይ ከአቅም በላይ የመጠቀም ሁኔታዎች እየጨመረ መሄዱን፣ ከሀረማያ ከተማ የሚለቀቁ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች በሀይቁ ደህንነት ላይ ከፍተኛ ሥጋት የደቀኑ መሆኑን እየተስተዋለ በመሆኑ የዩኒቨርሲቲውን ጥረት ውጤታማ እንዳይሆን አድርጎታል፡፡

83. ዩኒቨርሲቲው በሐረማያ ሀይቅ ዙሪያ በርካታ ጥናትና ምርምር ማድረጉን መረጃዎች የሚያስረዱ ቢሆንም በጥናቱ ልክ የውሃ አጠቃቀሞች ከሀረማያ ከተማ አስተዳደር እና ከወረዳ አስተዳደር ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር የምርምር ውጤቱ በሀይቁ ደህንነት ላይ ለውጥ እንዲያመጣ ባለመደረጉ ከሀረማያ ከተማ አስተዳደር በተለያየ አካባቢዎች ወደ ሀይቁ ደረቅ እና ፈሳሽ ቆሻሻዎች እየተለቀቀ መሆኑን በተወሰነ ደረጃ በጥንቄ፣

በዳሞታ እና በበጨቄ የሀራማያ ተፋሰሶችን ለማልማት ጥረት የተደረገ ቢሆንም በተጠቀሱት ቦታዎች እና በሌሎችም አካባቢ የመሬት መሸርሸር በከፍተኛ ደረጃ በመከሰቱ በሀይቁ ህልውና ላይ ሥጋት ደቅኗል፡፡

**በዩኒቨርሲቲው የወጡ የምርምር ውጠታማነትን በተመለከተ፡-**

84. በዩኒቨርሲቲው የወጡ የምርምር ውጤቶች እና ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ ማህበረሰቡ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

85. ይሁን እንጂ በቨርሚ ኮምፖስት ቴክኖሎጅ ላይ ምርምር ማድረግ የጀመረው በ1996 ዓ.ም. ሲሆን በዚህ ጊዜ ውስጥ 10 ምርምሮች የተከናወኑ እና 4ቱ ለህትመት መብቃቱ ከተመራማሪ የተገለፀልን ቢሆንም ከ18 ዓመታት ቆይታ አንፃር የምርምር ውጤቱ ለማህበረሰቡ ተደራሽነቱ ገና በሙከራ ደረጃ የሚገኝ መሆኑ፣ ለአካባቢው አርሶ አደር የውሃ ቆጣቢ የመስኖ ቴክኖሎጂ ላይ ምርምር በማድረግ ለማህበረሰቡ ሥልጠና በመስጠት ተጠቃሚ ለማድረግ በዕቅድ የተያዘ ቢሆንም ቴክኖሎጂው ጅምር ካልሆነ በቀር ለተጠቃሚ ተደራሽ ያልተደረጉ መሆኑ፣ በእንስሳት እና የእንስሳት መኖ ዙሪያ የምርምር ውጤቶች ለማህበረሰቡ ተደራሽ በማድረግ ተጨባጭ ለውጥ ያልተመዘገበ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ከተመራማሪው በተሰጠው ቃለ መጠይቅ ምላሽ ለማወቅ ተችሏል፡፡

86. ስለሁኔታው ምርምር የሚመሩ ኃላፊዎች ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ እንደ ዩኒቨርሲቲው ብዙ ምርምር ተደርጎ እስከ ምዕራብ ሸዋ ተደራሽ የተደረገ መሆኑ፣ ይሁን እንጂ የቨርሚ ቴክኖሎጂ ሥራው አድካሚ እና የህብረተሰቡን አቅም የሚፈታተን በመሆኑ እንደ ሀገርም ብዙ ትኩረት ያልተሰጠበት መሆኑን ገልጸዋል፡፡

87. የዩኒቨርሲቲው የሥራ ኃላፊዎች ከላይ የተገለፀው ምላሽ ቢሰጡም የቨርሚ ኮምፖስት /የተፈጥሮ ሀብት ማዳበሪያው/ ቴክኖሎጂ በምን ምክንያት ተደራሽነቱ አዝጋሚ እንደሆነ በጥናት የተለየ ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

88. ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በምርምር የተገኘው ቴክኖሎጂዎች ለማህበረሰቡ ተደራሽ በማድረግ የማህበረሰቡ ችግር እንዲፈታ ጥረቱን አጠናክሮ በአሁኑ ወቅት ያለው የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ዋጋ የማህበረሰባችን አቅም እየተፈታተነ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው የበኩሉን አስታወፅዖ እንዳያበረክት ያደርገዋል፡፡

# ክፍል ሶስት

***መደምደሚያ***

89.*የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጥበቃ፣ ምርምር እና ምርምር ፈንድ አጠቃቀም ውጤታማ መሆኑ ሲገመገም የሚከተሉት የመደምደሚያ ሃሳቦች ላይ ተደርሷል፡፡*

**የአካባቢ ጥበቃ ምርምር ስራዎች** (Environmental research) **ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን በተመለከተ፡-**

- ✓ *የሀረማያ ዩኒቨርሲቲው በየዓመቱ የማህበረሰብ ፍላጉት ለማወቅ የዳሰሳ ጥናት የሚያከናውን ቢሆንም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ ቁጥር* 1/2011 *ዓ.ም እና በዩኒቨርሲቲው ሴኔት ሊጅስትሌሽን ላይ በተጠቀሰው መሠረት ትኩረት የሚሹ ጭብጦችን በየአምስት ዓመት ወቅታዊ አልተደረገም፡፡*
- ✓ *በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች የማህበረሰቡን ችግር መሠረት ማድረጉ እና የተገኙ የምርምር ውጤቶች ተደራሽነት ላይ ውስንነት ያለበት መሆኑ፣*
- ✓ *በምስራቅ ሀረርጌ ከፍተኛ  የፀረ-ተባይ ዝቃጭ በውሃ እና በጫት ምርቶች ላይ መኖሩን በጥናትና ምርምር የተለየ ቢሆንም ኬሚካሉ በሰውና በእንሰሳት ላይ የመጣው ዐሉታዊ ተፅዕኖ ተገምግሞ በሌላ አማራጭ ኬሚካል እንዲተካ አልተደረገም፡፡*
- ✓ *ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው/በክልሉ/ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት ለመጠበቅ በርካታ ጥናትና ምርምር እያከናወነ  ቢሆንም በምርምር የተገኘው ውጤቶች ተግባራዊ ማድረግ ላይ ውስንነት አለበት፡፡*
- ✓ *ዩኒቨርሲቲው በምስራቅ ሀረርጌ ያለው የተፈጥሮ ሀብት የባቢሌ—ዝሆን፣ የዳከታ ትክል ድንጋይ፣ የቁንዱዶ ተራራ ፈረሶች እና በጋራ ሙለታ ወረዳ የልጅ እያሱ እስርቤት ለቱርስት መስብ እንዲውል ለማድረግ የተለያየ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎበት ተግባራዊ እንዲሆን ጥረት እያደረገ ቢሆንም እስከ አሁን ተግባራዊ ያልተደረገ መሆኑ፣*

- ✓ የተራቆቱ የደንገን ተራራን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ዩኒቨርሲቲው ከአካባቢና የደን ልማት ኮሚሽን ጋር የመግባቢያ ሰነድ በመፈራረም በብር 10 ሚሊዮን በ1035 ሄክታር ላይ የሞዴል ደን የማልማቱ ስራ የጀመረ ቢሆንም የተያዘለት በጀት በወቅቱ ባለመለቀቁ የፕሮጀክቱ ሥራ እየተቋራረጠ መሆኑ፣
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በሀገር በቀል (የባህላዊ) ዕውቀት ላይ በርካታ ምርምሮችን ያከናወነ ቢሆንም ወደ ተግባር ተቀይሮ ማህበረሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን አልተሠራም፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በሀረር ጤና ኮሌጅ፣ ሕይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል እና ሐርሜ (የማይጅ) ጠቅላላ ሆስፒታል የሚወጡት ፈሻስ ቆሻሻ ማስወገጃ ፕላንት (Treatment plant) ባለማዘጋጀቱ አልፎ አልፎ የቆሻሻ ማከማቻ ታንከሮቹ እየሞሉ ወደ ማህበረሰቡ እየተለቀቀ ቅሬታ እየተፈጠረ መሆኑ፣ እንዲሁም ደረቅ የሕክምና ቆሻሻዎችን ለማስወገድ የሚያስችል ኢኒስኔሬትር ባለመኖሩ አካባቢን ሊበክል በሚችል መልኩ በማቃጠል እንዲወገድ እየተደረገ ነው፡፡
- ✓ ከሀራማያ ዩኒቨርሲቲ ዋና ግቢ የሚሰበሰቡ ደረቅ ቆሻሻዎች፣ ፕላስትኮች እና ካርቶኒዎች በጉድጓድ ውስጥ እየተቀበረ የሚወገድ ሲሆን ይህ ሂደት መልሶ ለመጠቀም(Recycle እና ወደ ኮምፖስት በመቀየር እና በኃይል ምንጭነት ለመጠቀም የማያስችል ነው፡፡

**የምርምር ሀብት አያያዝና አስተዳደር ውጤማነትን በተመለከተ፡-**

- ✓ በዩኒቨርሲቲው መንግስት በሚመድበው መደበኛ በጀት የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች ፊዚካል እና ፋይናንሻል አፈፃፀማቸው በየሩብ ዓመት፣ በየስድስት ወሩ እና በየዓመቱ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ አፈፃፀማቸው ተገምግሞ ግብረ-መለስ እየተሰጠ በተቀመጠላቸው የጊዜ ገደብ እንዲጠናቀቁ ያልተደረጉ ፕሮጀክቶች አሉ፡፡፡
- ✓ በውጪ የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ የምርምር ፕሮጀክቶች የአፈፃፀማቸው ሪፖርታቸውን ምርምሩን ለሚመሩት የሥራ ክፍሎች እና ለዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር ቀርቦ እንዲገመገሙ አልተደረገም፡፡
- ✓ ከግብርና ምርምር ኢንስቲትዩት በሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ የሚከናወኑ የምርምር ሥራዎች በዩኒቨርሲቲው የፕሮጀክት መመዝገቢያ ቅጽ ላይ ተመዝግቦ አፈፃፀማቸው ክትትልና ቁጥጥር አልተደረገም፡፡

- ✓ በዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥራ የሚያከናውኑ ተመራማሪዎች አስቀድሞ የወሰዱትን የምርምር ሥራዎች ሣያጠናቅቁ ተጨማሪ የምርምር ኮንትራት እየተሰጣቸው ነው፡፡
- ✓ በዩኒቨርሲቲው የምርምር ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲው ሲለቁ የደረሱበትን የምርምር ውጤት፣ የፋይናንስ ሪፖርት እና ቴክኒካል ውጤቶች አልፎ አልፎ ርክክብ ሣያደረጉ የሚለቁ አሉ፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው የምርምር ጥናት ኩረጃን ለመከላከል የሚያስችል ሶፍትዌር (Plagiarism Checker software) አለመዘጋጀቱ እና የምርምር አጀንዳዎች ድግግሞሽ እንዳይኖር ምርምር ከመጀመሩ በፊት ከሌላ የምርምር ተቋማት ጋር የተመረጡ አጀንዳዎች በጋራ የሚገመገሙበት ሥርዓት የለም፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው ለምርምር ሥራ የሚያከናወነው የኬሚካል የግዥ ሂደቱ በጣም የሚጓተቱና በወቅቱ የማይቀርብ ነው፡፡
- ✓ በዩኒቨርሲቲው የተጠናቀቁ ምርምሮችን ከነታሪካቸው ለመያዝ የሚያግዝ የተደራጀ የምርምር ውጤቶች የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡
- ✓ የዩኒቨርሲቲው የቤተሙከራ ባለሙያዎች ከሥራ ገበታቸው ሲቀያየሩ ሲጠቀሙበት የነበረው የቤተሙከራ ንብረት ርክክብ የማያደርጉ የሥራ ክፍሎች አሉ፡፡
- ✓ በዩኒቨርሲቲው ግቢ ውስጥ ከ100 በላይ ቤተሙከራ ያለ ቢሆንም በየጊዜው ወቅታዊ (Calibration) አይደረግም፡፡
- ✓ ከየቤተ-ሙከራ የሚወጡ ፈሳሽ ነገሮች የአወጋገድ ሥርዓታቸውን የሚያሣይ ካርታ(Map) የሌለ የለውም፡፡
- ✓ በዩኒቨርሲቲው የቤተ-ሙከራ ንብረቶችን (Laboratory Work shop) የሚጠግን አደረጃጀት የለውም፡፡
- ✓ የዩኒቨርሲተው ቤተሙከራ ለማሻሻል Haramaya university's Teaching Action for the improvements በ2021G.c እና Guideline for Laboratory Analytical Service Provision at Haramaya University February 2022 በረቂቅ ደረጃ ተዘጋጀ ቢሆንም ፀድቆ ተግባራዊ አልተደረገም፡፡

- ✓ በተለያየ ቤተሙከራ ብር 61,103,331.18 የሚያወጣ ንብረት ከ7 እስከ 15 ዓመታት በላይ ያለአገልግሎት እንዲቀመጡ ተደርጓል፡፡

**ዩኒቨርሲቲው የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚው ተደራሽ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እተሠራ መሆኑን በተመለከተ፡-**

- ✓ ዩኒቨርሲቲው በሀረማያ ሀይቅ ዙሪያ የሚደረጉ የመስኖ ውሃ አጠቃቀሞች የሀይቁን ደህንነት፣ የአፈርንና የእጽዋትን ዕርጥበት መሰረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በጥናትና ምርምር ላይ ያመላከተ ቢሆንም ከሀረማያ ከተማ አስተዳደር እና ከወረዳ አስተዳደር ጋር በመሆን የምርምር ውጤቱን ተግባራዊ ለማድረግ ከማህበረሰቡ ድጋፍ ባለማግኘቱ በሀይቁ ደህንነት ላይ ለውጥ እንዳይመጣ አድርጎታል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በቨርሚ ኮምፖስት ቴክኖሎጅ ላይ ምርምር ማድረግ የጀመረው በ1996 ዓ.ም. ጀምሮ ሲሆን ከ18 ዓመታት ቆይታ አንፃር የምርምር ውጤቱ ለማህበረሰቡ ተደራሽነቱ ገና በሙከራ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው አርሶ አደር የውሃ ቆጣቢ የመስኖ ቴክኖሎጂ ላይ ምርምር በማድረግ ለማህበረሰቡ ሥልጠና በመስጠት ተጠቃሚ ለማድረግ በዕቅድ የያዘ ቢሆንም ቴክኖሎጂው ለተጠቃሚ ተደራሽ አልተደረገም፤

የሚሉ ናቸው፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩት መደምደሚ ሀሳቦች በመነሳት ለችግሮቹ መፍትሄ ሊሆኑ ይችላሉ ያልናቸው የማሻሻያ ሀሳቦች በክፍል አራት ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

# ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሃሳቦች

90.በሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የአካባቢ ጥበቃ፣ ምርምር እና የምርምር ፈንድ አጠቃቀም አፈጻጸምን ውጤታማ ለማድረግ ያግዛሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሃሳቦች አቅርበናል፡፡

- ✓ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ እና በዩኒቨርሲቲው በተዘጋጀው ሴኔት ሊጅስትሌሽን መሠረት በአካባቢ፣ በክልል እና በብሔራዊ ደረጃ ቅድሚያ የሚሹ ችግሮችን በዳሰሳ ጥናት በመለየት የምርምር ጭብጦችን በየአምስት ዓመት ወቅታዊ ማድረግ  አለበት፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በአካባቢው/በክልሉ/ ውስጥ ያለው የተፈጥሮ ሀብት የባቢሌ—ዝሆን፣ የዳከታ ትክል ድንጋይ፣ የቁንዱዶ ተራራ ፈረሶች እና በጋራ ሙለታ ወረዳ የልጅ እያሱ እስርቤት ለቱሪስት መስብ እንዲውል ለማድረግ የተለያየ ባለሀብቶች እና ባለድርሻ አካላት ተሳትፎበት ተግባራዊ እንዲሆን እየተደረገ ያለው ጥረት ተጠናክሮ ሊቀጥል ይገባል፡፡ እንዲሁም የሚመለከታቸው የመንግስት አካላትም ለዕቅዱ መሳካት የድርሻቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በአትክልትና ፍራፍሬ በድሬደዋ ከተማ ቶሚ እርሻ እና በሀረማያ ዩኒቨርሲት ዋና ግቢ ራሬ ምርምር ጣቢያ እያከናወነ የሚገኘው የምርምር ውጤቶችን ለአካባቢ፣ ለክልል እና ብሎም ለአገሪቱ ተጠቃሚ ማህበረሰብ ተደራሽነትን ለማሳለጥ፣በምስራቅ ሀረርጌ አካባቢ የተራቆቱ መሬቶች መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ ከሚመለከታቸው የመንግስት መዋቅር(ከክልል እስከ ቀበሌ)፣ ከግብረ ሰናይ ድርጅቶች እና ከባለሀብቶች ጋር በቅንጅት በመሥራት የማህብረሰቡን ችግሮች ለመፍታት ሊሰራ ይገባል፡፡
- ✓ በሐረር አካባቢ በርካታ ባህላዊ መድህንቶች መኖሩን እና እነዚህም ለመጥፋት በመመናመን ደረጃ የሚገኙ መሆኑን በዩኒቨርሲቲው ምሁራን በጥናትና መርምር የተገለፀ በመሆኑ ሀገር በቀል ተፈጥሮአዊ ሀብት እንዳይጠፉ በአፋጣኝ ለባለሀብት

በማስተዋወቅ ወደ ዘመናዊ መድሃኒትነት እንዲቀየር እና ለእፅዋቶቹ ተገቢው እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ዩኒቨርሲቲው ሊሠራ ይገባል፡፡

- ✓ ዩኒቨርሲቲው በሀረር ጤና ኮለጅ፣ ሕይወት ፋና ሪፈራል ሆስፒታል እና ሐርሜ (የማይጅ) ጠቅላላ ሆስፒታል የሚወጡት ፈሻስ ቆሻሻዎች ለማስወገድ የሚያስችል ፕላንት(Treatment plant) እና ደረቅ የህክምና ቆሻሸዎችን ለማስወገድ የሚያስችል ኢኒስሌሬትር በማዘጋጀት ቆሻሻዎች አካባቢን በማይበክል መልኩ እንዲወገድ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መመሪያ ምርምር 1/2011 ዓ.ም አንቀጽ 3 በተመለከተው መሠረት አግባብነት ካላቸው የሥልጠና መስኮች ብቃት ያለው የክትትልና ግምገማ ቡድን በመቋቋም የምርምር ፕሮጀክቶች ጥራቱን በጠበቀ መልኩ እንዲከናወን ምርምሮች በየደረጀው ማለፍ ያለባቸውን ሂደቶች በትክክል ማለፉን በሁሉም በመንግስት መደበኛ በጀት፤በሀገር ውስጥ እና ከውጭ ሀገር በድጋፍ በሚገኝ ፈንድ የሚከናወኑ የምርምር ስራዎች ላይ የምዝገባ፤የፊዝካልና ፋይናንሻል ሪፖርቶች በየወቅቱ በማዘጋጀት ክትትል እና ግምገማ ሊከናወን ይገባል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው ለምርምር ሥራ የሚያስፈልገው ግብዓት አቅርቦትን በተመለከተ በምርምር ሂደቱ ላይ የሥራ መጓተትን በሚቀንስ መልኩ በጥናት በመለየት የሚሻሻልበትን ሥርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ በዩኒቨርሲቲው ለምርምር ኮንትራት የሚገቡት ተመራማሪዎች አስቀድሞ የወሰዱት የምርምር ፕሮጀክቶች ያጠናቀቁ እና ውጤታማ መሆናቸው በመገምገም ቀጣይ ኮንትራት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡
- ✓ የዩኒቨርሲቲው ተመራማሪዎች በተለያየ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲው ሲለቁ የደረሱበትን የምርምር ውጤት፣ የፋይናንስ ሪፖርት እና ቴክኒካል ውጤቶች ርክክብ ሣያደርጉ የለቀቁት ላይ በውል ስምምነቱ መሠረት ተጠያቅነትን ሊያሰፍን ይገባል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ ሥርዓትን በመዘርጋት እና የምርምር ሥነ-ምግባር ቦርድ በመቋቋም ምርምሮች የሥነ-ምግባር መርህን ተከትሎ እንዲሰሩ በማድረግ ተማአንነት ያለው የምርምር ሥራ እንዲከናወን ሊያደርግ ይገባል፡፡


- ✓ ዩኒቨርሲቲው የተደራጀ የምርምር ውጤቶች የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ስርዓት በመዘርጋትና በየጊዜው ወቅታዊ በማድረግ በሀገር ሀብት እና ከሌላ ሀገር በተገኘው የገንዘብ ድገፋ የተከናወኑ የምርምር ውጤቶች በቀላሉ ለመረጃ ተጠቃሚ አካላት ተደራሽ የሚደረግበትን ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ✓ የምርምር ውጤታማነት ከሚወስኑ ነገሮች ውስጥ አንዱ የቤተሙከራ አደረጃጀትን ስታንደርዱን ማዘመን፣ የቤተሙከራ መሣሪያዎች በየጊዜው ወቅታዊ(Calibration) ማድረግ፣ እና የባለሙያዎችን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ አለባበሶች(Safety clothes) መጠቀም በመሆኑ ዩኒቨርሰቲው ትኩረት በመሰጠት በተሙከራዎችን ዘመናዊ በማድረግ የምርምር ጥራት እና ውጤታማነትን ሊያስጠብቅ ይገባል፡፡ እንዲሁም በአገሪቱ ውስን ሀብት ተገዝተው ያለአገልግሎት የተቀመጡ የቤተ-ሙከራ ንብረቶች አገልግሎት የሚሰጡ ከሆነ አገልገሎት ወደ ሚሰጡበት ክፍሎች በማዛወር ሊጠቀመበት፣ አገልገሎት የማይሰጡ ከሆነ ደግሞ በመንግስት ንብረት አወጋገድ መመሪያው መሠረት ሊያስወግዱ ይገባል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው የሀረማያ ሀይቅ ደህንነት ለመጠበቅ በርካታ ጥናትና ምርምሮችን፥ የተፋሰስ ልማቶችን ባከናወነው መሠረት ከሚመለከታቸው የሀረማያ ከተማ እና ወረደ አስተዳደር ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር የምርምር ውጤቱ በሀይቁ ደህንነት ላይ ለውጥ እንዲያመጣ በማህበረሰቡ ዘንድ ግንዘቤ በመፍጠር ሀይቁ ደግም ለጥፋት እንዳይዳረግ ሊያደርግ ይገባል፡፡ እንዲሁም የተፋሰስ ልማቱ በተጠናከረ መልኩ የሚቀጥልበት ሆኔታዎች ሊያመቻች ይገባል፡፡
- ✓ ዩኒቨርሲቲው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት በምርምር የተገኘው ቴክኖሎጅዎች ለማህበረሰቡ ተደራሽ በማድረግ የማህበረሰቡ ችግር እንዲፈታ ጥረቱን አጠናክሮ ሊቀጥል እና በአሁኑ ወቅት ያለው የሰው ሰራሽ ማዳበሪያ ዋጋ የማህበረሰባችን አቅም እየተፈታተነ በመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ችግሩን ለመቅረፍ የበኩሉን አስታወፅዖ ሊያበርክት ይገባል፡፡

በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የዩኒቨርሲቲው የበላይ ሥራ ኃላፊዎች እና ሠራተኞች፤ እንዲሁም መረጃ የሰበሰብንባቸው የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች ለኦዲቱ ሥራ መሳካት ላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት


## የዩኒቨርሲቲው ድርጅታዊ መዋቅር

አባሪ-1



አባሪ- 2

## የጥናትና ምርምር የሥራ ክፍል ድርጇታዊ መዋቅር



**አባሪ- 3**

**የኦዲቱ ጭብቶችና መመዘኛ መስፍርት**

**የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት:-** *<u>የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ</u>*

**የኦዲት አካባቢ፡- የሀረማያ ዩንቨርሲቲ የአካባቢ ጥበቃ ምርምር ስራዎች እና የምርምር የፈንድ አጠቃቀም ውጤታማነት**

| **የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ** (Audit Issues) | **የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች** (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| **ሀ/የአካባቢ ጥበቃ ምርምር ስራዎች**(Environmental research)**ቀልጣፋና ውጤታማ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም፤** | 1. የዩኒቨርሲቲ የምርምር ጭብጦችን በብሔራዊ የምርምር አጀንዳ ከተለዩት ውስጥ ቅድሚያ የሚሹ ምርምሮችን በየአምስት ዓመቱ በመለየት ተግባራዊ ሊያደርግው ይገባል፡፡ |
| | 2. ዩኒቨርሲቲው የአካባቢያዊ ችግሮችን ሊፈታ የሚያስችል ስትራቴጅ እና በተዘጋጀው ሃገራዊ ፍኖተ ካርታ መሰረት ምርምር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 3. ዩኒቬርሲቲው በአካባቢው/በክልሉ ውስጥ ያለውን የተፈጥሮ ሀብት በጥናትና ምርምር በመለየት ህብረተሰቡ ተጠቃሚ እንዲሆን ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 4. ተመራማሪዎች በምርምርና ጥናቶቻቸው ለአገር በቀል እውቀት ትኩረት ሰጥተው ሊሠሩ ይገባል፡፡ |
| | 5. ዩኒቨርሲቲው በምርምር ሥራዎቹ ወይም በሁለገብ ሥራዎቹ ውስጥ ተገቢውን የአካባቢ ደረጃ በመተላለፍ አካባቢን ሊበክል ወይም በሌላ አካል እንዲበከል ሊያደርግ አይገባም፡፡ |
| | 6. ዩኒቨርሲቲው አርንጓዴ አሻራ ለአርንጓዴ ልማት ለመተግበር ቋሚ ደን የሚለማበትን ቦታ ከአካባቢው መስተዳደር በመረከብ በጥናት የተደገፈ ልማት ሊያካሄድ ይገባል፡፡ |
| | 7. ዩኒቨርሲቲው በሀረማያ ሀይቅ የጠፉ የዓሳ ዝርያዎች ላይ ጥናትና ምርምር በማድረግ ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ሊዘረጋ እና ሊተገብር |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ይገባል፡፡ |
| | 8. ዩኒቨርሲቲው በአፈር ጥበቃ፣ ውሃ እና ደን ልማት ላይ የምርምር ሥራዎች ለመስራት የሚያግዙ የምርምርና የስልጠና ማዕከላት ሊያቋቁምና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| ለ/የምርምር ሀብት አያያዝና አስተዳደር ውጤማነት መገምገም፡፡ | 9. ለየምርምር ፕሮጅክቱ የተመደበው በጀት በትክክል ለታለመላቸው ዓላማ መዋሉን በየጊዜው የፕሮጀክቶቹን ፊዝካል እና ፋይናንሽል አፈፃፀም ግምገማና ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 10. ዩኒቨርሲቲው በምርምር ትኩረት አቅጣጫዎች ስር ያሉ የምርምር ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜ እና በጀት መሰረት ስለመጠናቀቃቸው ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርገው ይገባል፡፡ |
| | 11. ዩኒቨርሲቲው ለምርምር ስራዎች የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን በወቅቱ ሊያሟላ ይገባል፡፡ |
| | 12. የምርምር ሥራ የሚያከናውኑ የሥራ ክፍሎች የሥራ ክንውናቸውን የሚያሣይ ሪፖርት በየሩብ፣ በየስድስት ወሩ እና በየዓመቱ በማቅረብ ሊያስገመግሙ ይገባል፡፡ |
| | 13. ዩኒቨርሲቲው በምርምር የወጡ ውጤቶች ያስገኙት ለውጥ ለማወቅ በየጊዜው የዳሰሳ ጥናት ሊያከናውን ይገባል፡፡ |
| | 14. በዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥራ ለማከናወን ኮንትራት የሚገቡት ተመራማሪዎች አስቀድሞ በወሰዱት ኮንትራት |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ላይ ውጤታማ መሆናቸውን ከተረጋገጠ በኋላ ሌላ የምርምር ኮንትራት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ |
| | 15.የዩኒቨርሲቲው የምርምር ባለሙያዎች በተለያየ ምክንያት ከዩኒቨርሲቲው ሲለቁ የደረሱበትን የምርምር ውጤት፣ የፋይናንስ ሪፖርት እና ቴክኒካል ውጤቶች ርክክብ የሚደረግበት ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 16.ዩኒቨርሲቲው ለተለያዩ ምርምር ዘርፎች ፈንድ እና ድጋፍን የሚስተዳድር የሥራ ክፍል ሊያቋቁምና በየሩብ ዓመት፣ በየስድስት ወሩ እና በየዓመቱ አፈፃፀሙን ሪፖርት ሊያቀርብ ይገበል፡፡ |
| | 17.የኒቨርሲቲው የምርምር ሀብት ለማስተዳደር የሚያግዝ የአፈፃፀም መመሪያ ሊያዘጋጅና ተግባራዊ ሊያደርገው ይገባል፡፡ |
| | 18.በተለያዩ የዩኒቨርሲቲ መምህራን አማካይነት የሚመጡ በውጭ ድርጅቶች የሚደገፉ ፕሮጀክቶች ወደ አንድ ቋት እንደ ተቋም እንዲመዘገቡና ለታለመለት ዓለማ መዋሉን ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 19.ዩኒቨርሲቲው የሚሰጣቸው የግራንቶች ውድድሮች ህጋዊ ሂደታቸውን የጠበቁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 20.ለዩኒቨርሲቲው ምርምር ስራ የሚመደቡ ፕሮጀክቶች ወደ ስራ ከመግባታቸው በፊት የተሟላ የውል ስምምነት ሊዘጋጅላቸው ይገባል፡፡ |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 21.ዩኒቨርሲቲው ለምርምርና ጥናት ስራዎች አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶችን በወቅቱ ለማቅረብ የሚያስችል የግዥ ስርዓት በመዘርጋት ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |
| | 22.ዩኒቨርሲቲው የተለያዩ የምርምር ስራዎችን ለመስራት የሚያግዙ ላብራቶሪዎችን ማደራጀትና ማዘመን አለበት፡፡ |
| ሐ/ የምርምር ውጤቶች ለተጠቃሚው ተደራሽ ለማድረግ ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ መሆኑን መገምገም | 23.ዩኒቨርሲቲው የምርምር ሥነ-ምግባር መቆጣጠሪያ ሥርዓትን በመዘርጋት የምርምር ጥናት ኩረጃን(Plagiarism Checker software) እና አንድ የምርምር ሥነ-ምግባር ቦርድ በመቋቋም ምርምሮች የሥነ-ምግባር መርህን ተከትሎ እንዲሰሩ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 24.የተደራጀ የምርምር ውጤቶች የመረጃ አያያዝ እና አስተዳደር ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 25.በዩኒቨርሲቲው የሚከናወኑ የአካባቢ ምርምር ስራዎች የህብረተሰቡን ፍላጎት መነሻ ያደረጉና ችግር ፈቺ ሊሆኑ ይገባል፡፡ |
| | 26.በዩኒቨርሲቲው የወጡ የምርምር ውጤቶች እና ቴክኖሎጂዎችን ተግባራዊ በማድረግ ማህበረሰቡ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 27.ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው አርሶ አደር የውሃ ቆጣቢ የመስኖ ቴክኖሎጅ ላይ ምርምር በማድረግ ተጠቃሚ እንድሆኑ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 28.ዩኒቨርሲቲው የሐራማያ ሐይቅ የመጠበቅና የማስቀጠል |

| የኦዲት ትኩረት አቅጣጫ (Audit Issues) | የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | ሥራዎች ከአካባቢው ማህበረሰብና ከከተማ አስተዳደር ጋር ጥብቅ ቁርኝት በመፍጠር የሐይቁን ህልውና ሊያስቀጥል ይገባል፡፡ |
| | 29.ዩኒቨርሲቲው በቨርሚ ኮምፖስት እና የአፈር ለምነትን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጅዎች ላይ ምርምር በማድረግ ለተጠቃሚዎች ተደራሽ የሚደረግበት የአሠራር ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 30.ዩኒቨርሲቲው ለአካባቢው ማህበረሰብ የዘር ጥራት ማረጋገጫ ሥራ በመስራት ለዘር አምራቾች ማህበራት እንዲሰራጩ ሊያርግ ይገባል፡፡ |
| | 31.የተሰሩ የምርምር ስራዎችንና ውጤቶችን በዩኒቨርሲቲው ድህረ ገጽ በማደራጀት ለተጠቃሚ ተደራሽ ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 32. ዩኒቨርሲቲው ከሌሎች ዩኒቨርሲቲዎች እና የምርምር ተቋማት ጋር በመቀናጀት ምርምር ሥራዎች ድግግሞሽ እንዳይኖር በጋራ ሊጠቀሙባቸው የሚያስችላቸውን የመረጃ አያያዝ ሥርዓት ዘርግቶ ተግባራዊ ሊያደረግ ይገባል፡፡ |

**አባሪ -4**

## የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ ስድስት ዋና ዋና የምርምር መስኮች

| ተ.ቁ | የምርምር ትኩረት መስኮች |
|---|---|
| 1 | ምርታማነት አካባቢ ጥበቃና የምግብ ዋስትና የምርምር ትኩረት መስክ (Theme I) |
| 2 | ጤናና ስነ- ምግብ የምርምር ትኩረት መስክ (Theme II) |
| 3 | ኢነርጂ፣ ኢንጂነሪንግ ና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (Theme III) |
| 4 | ህብረተሰብና ማህበረሰብ ልማት ምርምር ትኩረት መስክ (Theme V) |
| 5 | የተቋማት የፈጠራ ሥራ አካሄድ ና የኢኮኖሚ ልማት የምርምር ትኩረት (Theme IV) |
| 6 | የመሠረታዊ ሣንስ የምርምር ትኩረት (Theme VI) |

### የሀረማያ ዩኒቨርሲቲ የምርምር ጣቢያ ዝርዝር

| ተ.ቁ | የምርምር ጣቢያው ሥም |
|---|---|
| 1. | ራሬ የምርምር ጣቢያ |
| 2. | ሐረማያ የእንስሳት ምርምር ጣቢያ |
| 3. | ሐረማያ የበጎች ምርምር ጣቢያ |
| 4. | ሐረማያ የፍያል መርምር ጣቢያ |

| | |
|---|---|
| 5. | ባቢሌ የቆላ ቅባት የምርምር ጣቢያ |
| 6. | ኤረር በርከሌ የአትክልት ምርምር ጣቢያ |
| 7. | ኤረር ጉዳ የግማል ምርምር ጣቢያ |
| 8. | ሂርና የደጋ ሰብል  የምርምረ ጣቢያ |
| 9. | ፈዲስ የቆላ ሰብል ምርምር ጣቢያ |
| 10. | ጉራዋ የድንች ምርምር ጣቢያ |
| 11. | ኩርፋ ጨሌ የሰብል ምርምር ጣቢያ |
| 12. | ጉራዋ አፕል ምርምር ጣቢያ |
| 13. | ድሬዳዋ አትክልት ምርምር ጣቢያ |
| 14. | ቀርሳ ጤናና ስነ ህዝብ ሥርዓተ ቅኝት ምርምር ጣቢያ |